Harla J. Soc.Behav. Studies 2022 1(2):81-98

Harla Journals

Harla Journal of Social and Behavioral Studies

Journal home page: https://journals.ddu.edu.et/index.php/HJSBS

Harla journal of Social and Behavioral Studies

# ክስተተአካላዊ የአብዮት ዘመን ማህበረግለሰብ ማንነት አመሳሰል በ‹‹መረቅ››

**ይድነቃቸው ሰለሞን** [1]

*የእንግሊዝኛ ቋንቋ እና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ደብረ ብርሀን ዩኒቨርሲቲ* **Email፡-** ahaduyid2000@gmail.com

## አጽህሮተ ጥናት

*የዚህ ጥናት አላማ በአዳም ረታ* ***‹‹መረቅ››*** *ረጅም ልቦለድ ድርሰት ገጸ-ባህሪያት ክሱት የሕይወት ተሞክሮ ዘልቆ በመግባት የአብዮት ዘመን ማህበረግለሰብ ማንነት አመሳሰልን ከማህበራዊ ሥነ-ምግባርና ከስነ-ልቦና መነሻዎች አንፃር በፍካሬ ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ሲሆን በንባብ የሰነድ ፍተሻ ዘዴ እና በአላማ ተኮር ንምና ዘዴ መረጃውን አጠናቅሮ በይነ-ዲሲፐሊናዊ ትንተናን እንደመፈከሪያ ስልት ይጠቀማል፡፡ እንዴት ቢሉ? ጥናቱ አላማውን ከግብ ለማድረስ ተንታኝ ሥነ-ትርጉማዊ ክስተተአካል የጥናት ሥነ-ዘዴን በፍካሬልቦና (Psychoanalysis) በሃዲስ ታሪካዊነት (New Historicism) እና በስነ-ማህበረሰብ (Sociology) እሳቤዎች እያታገዘ ድርሰቱን ለመመርመር ይሞክራል፤በይነ-ዲስፐሊናዊ ፍካሬ ለዚህ ጥናት የተቀመረው የክስተተአካላዊ ሥነ-ዘዴ ባህሪይን፣ ለአጥኚው የሚፈጥረውን አንፃራዊ ነፃነት እና የጥናቱ አተኩሮት የሆነውን የነገረ-ማንነትን ውስብስብነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ጥናቱ ገጸ-ባህሪያኑ በሥነ-ምግባር ደረጃ ከማሕበራቸው እንደሚወጡ አመላክቶል፡፡ ይህምየተመለከተው ማህበረሰብ ጤናማ አይደለም በሚል ተተርጉሟል፡፡ የላካንን ቋንቋ መር የፍካሬ-ልቦና እስብ ላይ ተመስርቶ በተካሄደው ትንተናም በግለሰባዊ ሥነ-ልቦና ደረጃ ገጸ-ባህሪያኑ ሃሳባቸውን፣ ስሜታቸውን፣ ፍላጎታቸውን መግለፅ እንደከበዳቸውና መግለፅ የሚችሉት/ የተረዱትን ደግሞ በነጻነት ወይም በድፍረት ከመግለጽ እንደሚታፈኑ አሳይቷል፡፡ ይህም በግለሰብ ስብዕና ደረጃ የታጎለ ሥነ-ልቦናን አመላካች ተደርጎ ተወስዷል/ተተርጉሟል፡፡ ድርሰቱ የበቀለበት የአብዮት ዘመን የታፈነ ማህበረሰብ እና የተቃወሰ ግለ-ሰብ ሆኖ መመሰሉን ጥናቱ ያሳያል፡፡ስለዚህም ጥናቱ በ‹‹መረቅ›› የአብዮቱ ዘመን* ***ማህበረግለሰብ ማንነት የተመሰቃቀለ ነው የሚል ክስተተካለዊ መደምደሚያ ያቀርባል፡፡*** *ጥናቱ በይነ-ዲስፐሊናዊ የሥነ-ጽሁፍ ጥናት ጥሪ ለሥነ-ጽሁፍ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የጥናት መስኮች እንደሆነ የሚጠቁም ነው፡፡ያሁኑ ጥናት ጥቅም የቋንቋና ሥነ-ጽሁፍ ምርምር በአገራችን ሁለንተናዊ እድገት ሊወጣ የሚችለውን ሚና በማመላከት ተጠናክሮ እንዲቀጥል መጠቆም ነው፡፡*

*The purpose of this study is to scrutinize the life experience of the characters in Adam Reta's long novel 'Mereq' and show the representation of the social and individual identities during the revolution period in terms of social ethics and psychological origins. The study is qualitative and collects the data by document inspection method and purposive sampling method, and uses interdisciplinary analysis as a strategy. To achieve objectives, the research tries to analyze the essay by using the analytical, semantic, phenomenological method of psychoanalysis, New Historicism, and Sociology. This is by considering the relative freedom it creates and the complexity of the science that is the focus of the study. The research shows that the characters are morally out of their society; this means that the society in question is not healthy. In the analysis based on Lacan's view of psychoanalysis, the study showed that at the level of individual psychology, the characters find it difficult to express their thoughts, feelings, and desires, and what they can express was that they are suppressed from expressing freely or boldly. This has been interpreted as an indication of a heightened psychology at the individual personality level. The study also revealed that the revolution period in which the novel was born was like a suppressed society and a protested individual. Therefore, the study presents a conclusive argument that the society and individual identity of the revolution period is chaotic. Furthermore, the study suggests that the call for interdisciplinary literary research is not only for literature, but also for other fields of study. The present study is to indicate that the role that language and literature research can play in the overall development of our country.*

***ቁልፍ ቃላት፡-*** *ማህበረ-ግለሰብ፣ የአብዮት ዘመን፣ ማንነት፣ አመሳሰል*

*Corresponding author: ይድነቃቸው ሰለሞን, email, ahaduyid2000@gmail.com phone,+251900352336*

*DOI:*
*© 2022Harla Journals and Author(s). Published by Dire Dawa University on Open Access Policy under CC-BY-NC 4.0.*
*Received month year, September 2022; Received in revised form month year, November 2022; Accepted month year, December 2022.*

## 1. መግቢያ በንድፈ ሃሳባዊ ቅጥ

በማህበረሰብ ትምህርት ውስጥ ግለ-ሰብ እና ማህበረሰብ ስለማይነጣጠሉ ማህበራዊነት ለሰው ልጅ ዋናው የማንነት መገለጫው ነው፡፡ ይህ ማህበራዊ የሰው ማንነት በግለ-ማህበረሰቡ ስልጣኔ እና ዘመን የሚበየን ነው፡፡ እንደ ሥቱዋርት ሆል (Stuart Hall) ማንነት የሚገነባውም በግለሰቡና በማህበረሰቡ ማሃከል በሚደረገው ቀጣይነት ባለው ምልልስ (interaction) ነው፡፡ ሆል «One is in a "continuous dialogue with the cultural worlds 'outside' and the identities which they offer"» … እንዳሚለው ማለት ነው፡፡ ባርከርም "Idenity… bridges the gap between the 'inside' and the 'outside'- between the personal and the public worlds… making both reciprocally more unified and predictable." በማለት ማንነት ግለሰቡ (the subject) በመወለድ፣ በማደግና በመኖር ከማህበረሰቡ የሚወስደውና በማሻሻል መገለጫው የሚያድረገው ስለመሆኑ አስረድቷል፡፡ በዚህ ኡደታዊ ሂደት የስልጣኔ ምንጭ ግለሰቡ ሲሆን ማረፊያው ማህበረሰቡ ይሆናል[1]፡፡

ባለኝ ንባብ፣ ጉዳዩን ለመጀመሪያ ግዜ ያመላከተው ሶሲዎሎጂስቱ ፓሬቶ ሲሆን እንደፓሬቶ እስብ ማህበረሰብ እርስ በእርስ በተሳሰሩ ክፍሎች እና አስተካካይ ለውጦች ይመራል፡፡ ፓርሶን የፓሬቶ ሃሳብ ላይ በመመስረት ይህ ተንቀሳቃሽ ሚዛኑን የጠበቀ የመንፈስ አርጋታ ማህበረሰቡን ሰላም የሰፈነበት፣ መንፈስ የሚታደስበት፣ እርስ በእርሳቸው የሚናበቡ እና የሚግባቡ ግለሰቦች የበዙበት ያደርጉታል፤ "moving equilibrium that produces harmony for the system," (Pareto, V (1948-1929) cited in Wallace, A and Wolf, A 1995: 21)፡፡

ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት ነው **<u>ማህበረግለሰባዊ ማንነት</u>** በሚል ርዕስ የተቀኘ ሃተታ ለማቅረብ መወጠኑ፡፡ ይህ አይነቱ ማንነት በስልጣኔ የፈጠራ ጥበብ እየተመራ በአዲስ/የተሻለ የህይወት መስመር እየተቃኘ እየተሻሻለ የሚሄድ ነው፡፡ ቦታ የማንነት መቀንበቢ እና ዘመን የማንነት መለኪያው ነው፡፡ ስለዚህም ነው ሃገራችን ያለፈችበትን **<u>የአብዮት ዘመን</u>** መጥቀስ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ እንደ ቴዎድሮስ (2001፤ 153) ሰውን ከማህበራዊ፣ ከስነ-ልቦናዊና ከስነ-ምግባዊ ማንነቱ አንጻር ለመበየነ መነሳሳት እሱነቱን አጉልተውና አግዝፈው ማንነቱን በጥልቀት የማየት እድል ይፈጥራል፡፡

ስለዚህም በመጀመሪያው ክፍል ክስተተአካላዊ ማንነት ከማህበራዊ መነሻዎች አንጻር ተከስቶ ትንታኔ የቀረበበት ሲሆን ማህበራዊነትን ከእምነት አንፃር፣ ማህበራዊውን እምነት/ሃይማኖት ከሥነ-ምግባር አንጻር የተበየነበት ነው፡፡ ምክንያቱም፣ ሃይማኖት «የየትኛውም ማህበራዊ ተቋም መጠሪያ ነው፡፡ ሃይማኖት ተከታዮቹ የሚተዳደሩበትን የስነ ምግባር ደንብ ይጥላል፡፡ ኑሮአቸውን የሚጥሉበት የህይወት ፍልስፋና፣ ዓለምን የሚያዩበትና የሚመዝኑበት፣ የሚገሩበትና የሚያሸንፉበት ርእዮተ አለምም አለው፡፡» (ቴዎድሮስ፣ 2001፤ 254)፡፡ በክፍል ሁለት ክስተተአካለዊ ማንነት ከሥነ-ልቦናዊ መነሻዎች አንጻር ተከስቶ ትንታኔ ቀርቦበታል፡፡ በዚህ ክፍል የላካን የፍካሬ-ልቦና እስቦች ለጥናቴ ግብ መታመን የሚያበረክተውን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለመተንተኛነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደረጓል፡፡ ስለሆነም በድርሰቱ የምናገኛቸው መሪ ገጸ-ባህሪያት ላይ ተናጥላዊ የስነ-ልቦና ትንታኔ ቀርቧል፡፡

በሃገራችን ሥነ-ፅሁፍ ጥናት ባለሙያ የሆነው ቴዎድሮስ ገብሬ የአማርኛ ልቦለድና ፍካሬ ልቦና ጎረቤታሞች ሳይሆኑ አብሮ አደግ ጓደኛሞች እንደሆኑ ያምናል፡፡ ጠንከር ባለአገላለጽም የአማርኛ ልቦለዶች «አፍ አውጥተው» በፍካሬ ልቦና እንዲመረመሩ «የሚማጸኑ» ስለመሆናቸው በጥናቶች ግኝት አስደግፎ ያቀርባል፡፡ ሁለቱም ቋንቋ መር ሳይንሶች መሆናቸውንም ያሰምርበታል፡፡ ለአብነትም ተማሪው <u>ቴዎድሮስ አለበል</u> (2006፤ 22) እንዳስቀመጠው ሥነ-ጽሁፍና ሥነ-ልቦና በሰው ልጅ ማንነትና በትዕምርት አፈጣጠርና አጠቃቀም ላይ የሚያነጣጥሩ በመሆናቸው ዝምድናቸው ገናን ነው፡፡

> ወዲህ ግላዊ ማንነቶች ላይ ጥናታቸውን ያነጣጥራሉ፤ ሥነጽሑፍ ገፀ-ባህሪያትን እንደግለሰብ እንጂ እንደስብስብ ወስዶ አይጨፈልቅምና፡፡ ወዲህ "ወላዊ" እና ግለሰባዊ ጉዳዮችን በትዕምርት ለመመርመር የሚሞክሩ ናቸው፤ ሥነጽሑፍ ፍቺን እና የኪናዊዋ ጋን፣ ሥነልቡና ደግሞ የልቡናዊ መታጎሎችን (Psychical Disorder) ምንጭ ለመፈለግ፡፡ ስለሆነም ዝምድናቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ (ቴዎድሮስ 2006፡22)፡፡

አድማሰ ሰፊው ሥነ-ጽሁፍ የሳይንሶችን ድንበር ደምስሶ ረቂቁን የህይወት እውነት ማሳየት እንደሚችልም ተመስክሮለታል፡፡ በመሆኑም አንድን የሥነ-ፅሁፍ ስራ በተለያዩ መነፅሮች ለማጥናት መሞከር ግዳጅ ነው፡፡ ምክንያቱም "በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ-ፅሁፍ ጥናት …ለምናብ ነፃነትን ይሰጣል፡፡ ለፈጠራ ንባብም ቀና ነው፡፡ ከዚህ አይነቱ ንባብ ደግሞ ሥነ-ውበታዊ፣ ርዕዮተ አለማዊ፣ ፍልስፍናዊ፣ ወዘተ አንድምታዎችን ማዘመሩ እምብዛም አይከብድም፡፡" ፤ ቴዎድሮስ (2001፤xii) ፡፡

[1]ሆልና ባርከር ሃሳብ የተወሰድው Explication on Lacanian Psychoanalysis በሚል ርዕስ በNational Chengi University Liberary ከመረጃ መረብ የተወሰደ ነው፡፡

ጥናቱ በሦስት ዋና ነጥቦች የተቀነበበ ነው፤ የመጀመሪያው የማህበራዊ ለውጡ እና መዘዞቹ (በተለይም ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ጣጣው) በቅጡ አለመታየቱ ሲሆን በዚህ ረገድ ከግል አስተያየት ያለፈ ጥናቶች እምብዛም አይገኙም፡፡ ይህን ጥናት ክፍተቱን የማጥበብ ስራ ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ሁለተኛው፣ ደራሲው ለሃገራችን ባህል የሚቸረውን ግዙፍ ስፍራ እና በፍካሬልቦና በሚያቀርበው ሥነ-ጽሁፋዊ ተረክ የተመሰከረለትና በመሆኑ ነው፡፡ በ**አዳም** አጭር ልቦለዶች ላይ ቴዎድሮስ አለበል (2006) ባቀረገው ጥናት መደምደሚያ የሰነዘረውን መካሪ ሃሳብ አለ[2]፡፡ ድርሰቱ የቀረበበትን ቴክኒክ ከግምት ውስጥ አስገብቶ ለሥነ-ዘዴው አመቺ ሆኖ መገኘቱ ሦስተኛው ነው[3]፡፡

## 2. **የጥናቱሥነ-ዘዴ**

> "Phenomenological research characteristically starts with concrete description of lived situation, often first person account, set down in everyday language and avoiding abstract intellectual generalizations. The researcher proceeds by reflectively analyzing these descriptions, perhaps ideographically first, then by offering a synthesized account, for example identifying general themes about the essence of a phenomenon. Importantly, the phenomenological researcher aims to go beyond surface expressions or explicit meanings to read between lines so as to access implicit dimensions and intuitions." Finlay, L (2009፡ 10)

ክስተተአካል Phenomology በኤድሙንድ ኸርስል የገነነ አካልን (Being) በተገለጠበት መንገድ እየከሰቱ ምንነቱን ባልተበረዙ ንቁ ተመስጦዎች፣ ውህደቶች፣ አመለካከቶች፣ ንጥረ-ነገሮችና ቁስ አካሎች መተንተንን «ብቸኛው» የዕውቀት ምንጭ ያደረገ የፍልስፍና አብዮት ነው (ሰምነር፣ 1989፣ 244)፡፡እሳቤው ከፍልስፋና ምህዋርነቱ ባሻገር በሃኛ አንደኛው ክፍለ-ዘመን ለተለያዩ ዲስፒሊኖች በተለይም ለፍካሬልቡና፣ ለሶሲዎሎጂ፣ አንትሮፖሎጂ፣ ለታሪክ እና ሥነ-ጽሁፍ፣ ለፖለቲካ፣ ለጤና ወዘተ. ትምህርት ዘርፎች የጥናት ዘዴ ለመሆን ችሏል፡፡ እንደ ጥናት ዘዴ በተለያዩ ምሁራን የተሰጡ ብያኔዎችን በማጥናት ካፍሊ (2011) ሲፅፍ ክስተተአካል የግለሰብ የሕይወት ተሞክሮን በጥልቀት ሰጥሞ በማጥናት ተሞክሮውንበትክክለኛው መንገድ ልክና መጠን የሚያቀርብ ነው፡፡ *[The] definitions of phenomenology offered... focus that it is phenomenology that has the potential to penetrate deep to the human experience and trace the essence of a phenomenon and explicate it in its original form as experienced by the individuals. (Kafle, 2011:183)::ሥነ*-ዘዴው ሶስት መሪ እሰቦችን ያቅፋል፡፡ እነዚህም 1.ፍጹማዊ ክስተተኣካል (Transcendental Phenomenology)፣ 2.ሥነ-ትርጉማዊ ክስተተአካል (Hermeneutic Phenomenology)፣ እና 3. ህልውናዊ ክስተተአካል (Existential Phenomenology) ናቸው[4]፡፡ በፍጹማዊ ክስተተአካል ተግባራዊ ቅጥ (Framework) የተዋቀረ ጥናት ዋናነጥብ /አላማ/ግላዊነትን አስወገዶ አካሉ በተከሰተበት መንገድ፣ ልክና መጠን በመግለጥ/በመከሰት እና በመተንተን የአካሉን መሰረታዊ መገለጫ ባህሪያት (essence)ማግኘት ነው፡፡በሌላ በኩል የምናገኘው ሥነ-ትረጉማዊ ክስተተአካል ግላዊነትን በጋበዘ መልኩ የአካሉን መሰረታዊ መገለጫ ያለመ ነው፡፡

እንደ ፊንሌይ እና ላንድሪጅ በከሳች እና በተንታኝ መካከል ቋሚ መስመር/ ድንበር እንደሌለ እና ሁለቱን ምልከታዎች በአንድ መስመር ላይ እንደሚገኙ ተከታትሎዎች መታየት እንዳለባቸው ይመከራሉ፡፡ በሌላ በኩል፣ ትንታኔውን ማብዛት ክስተተአካልን ሥነ-ትርጉማዊ ወይም ትንታውን ቆጥቦ በማሳነስ አካሉን ማመላከት ጥናቱን ፍጹማዊ ክስተተአካል ሊያደርገው ይችላል የሚል አስተያየትም አለ፡፡ እንደ ሪኮር በተጨማሪ ውቅረ-መስክ/ቅጥ (framework) ፤ (ለምሳሌ ፍካሬልቡናን ይጠቅሳል) ሃተታ የታገዘ የክስተተአካል ጥናት ሥነ-ትርጉማዊነቱ ይጎላል፣ (በፊንሌይ 2009፡ 11 የተጠቀሰ)፡፡ፍንሌይ (2009) ሐይዲጋርን ጠቅሶ እንዳስቀመጠው «አካሉን መከሰት በራሱ ሥነ-ትርጉማዊ ሂደት» በመሆኑ ከሳች ከሆነው ፍጹማዊው ክስተተአካል እሰብ ይለያል፡፡ በመሆኑም፣ ለነገሮች ትርጉም መስጠት ተጨማሪ

---

[2]*አዳም (***በማሕሌትና አለንጋና ምስር***) ሥነልቡናዊ ጽንሰሃሳቦችን ኢያለመደ እንደሚፅፍ፣ እነዚህን ጽንሰሃሳቦች ለማልመድ ባህላዊና ሚታዊ አስተማስሎዎችን እንደኪናዊ "ተውህቦ" ማላቂያ እንደሚጠቀም፣ ... በቴክስቶቹ ውስጥ ታሪካዊ ክስተቶች፣ ኢጅግ የገነኑ ማኅበራዊ ጉዳዮችና ስዕል ሰርካዊ ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ ሥራዎቹን ከ"ባህልጥናት"፣ ከሥነማኅበረሰብ እና ከ"ታሪክ" አንጻሮችን አልምደው፣... ቢያጠኗቸው* አዋጭነታቸው ላቅ ያለ ይመስለኛል፡፡ (ቴዎድሮስ አለበል፤ 2006፤ 70-71).

[3] ሥነ-ዘዴውን አስመልክቶ በክፍል ሁለት የሚመጣውን በፊንላይ (Finaly, Linda 2009፡ 10) የተሰነዘረ ሃሳብ እንደ ማሳያነት እንመለከት

[4]ፍጹማዊ ክስተተአካል በጠንሳሹ ሀርስል የተቀነበበው ሲሆን በእዚህ እሰብ እውነታ አንድ እና አንድ ብቻ ነው፤ ፍፁምነት ያለው፤ የሚደረሰውም ይሁነኝ ተብሎ በነቃ ተመስጦ (pure conscious) እና ጥርጣሬን ቀነሶ ግልፅ ለመሆን ግላዊ ሃሳቦችን በቅንፋዊ (bracketing) ስልት በማስወገድ ይሆናል፡፡ የሥነ-ትርጉማዊ ክስተተአካል መነሻ በቋንቋ አለም እና በማህበራዊ መስተጋብሮች በመዋጣችን የተነሳ እንዲሁም ከታሪካዊ ግንዛቤዎች ውጭ ባለመሆናችን ምክንያት ስለነገሮች እና ስለእራሳችን ትርጓሜ መስጠት የግድ መሆኑ ላይ ነው፡፡የህልውናዊ ክስተተአካልየቃሉን ብያኔ ከቴዎደሮስ ገብሬ 136፣ 2001 የተወሰደ ሲሆን አንድምታው በፍልስፍና ነገረህላዌን በሚያጠብቁ ፈላስፎች የተመራውን የህልውናዊነት ንቅናቄ የሚያሳይ ነው፡፡

አካሄድ ሳይሆን የማይቀረውን የአካሉን ዋና መዋቅር በአለም ውስጥ መገኘት (being-in-the-world) ትርጉሞ መተንተን ነው፡፡ዝኒ ከማሁ፡፡

የሥነ-ትርጉማዊ ክስተተአካል እሰብ በግለሰባዊ እና ቡድናዊ ገለ-ተሞክሮ ላይ የተንጠለጠለ ሲሆን የጥናቱ ኡደት (አካሄድ) ግንበፍልስፍናዊ ሃተታ የተቃኘእንዲሆን ይጠበቃል (ካፍሌይ 2011፡ 188)፡፡ በግለ-ተሞክሮ ትርጓሜ እውነተኛውን እና ተጨባጭ የሆነ የነገሮችን ባህሪ ማፍለቅ የእስቡ የመጨረሻ አላማው ነው፡፡የእስቡን አመዕክኖ ፊንሌይ (2009፡ 12) ጊዎረጊን ጠቅሶ እንዳስቀመጠው ምንም ነገር ከግለሰባዊ እይታ ውጭ ሊከወን ስለማይችል ግላዊነቱን ለማስወገድ መሞከሩ ውሃ አያነሳም፡፡ ቁምነገሩ የአካሉ/ የጉዳዩ አቀራረብ ሲሆን ተጨባጭነት (objectivity) የግለሰብ ውጤት ነው፡ ሆኖም አጥኚው ክስተተአካላዊ አመለካከቱን (phenomenological attitude) በመጠቀም ዙሪያገባውን ለመመልከት ክፍት በመሆን ሕይወትን በሌላ ጎኑ ለመመልከት መሞከር ይኖረበታል፡፡ በሂደትም አትኩሮቱን በዋናው አካል ላይ ማኖር ይጠበቅበታል፣ ወደ ተነሳበት አላማ መመልከት መቻል ይጠበቅበታል ማለት ነው (ዝኒ ከማሁ)፡፡

እንደ ኢታዎ የመጀመሪያው ግልፅ ያልተቀመጠውን ነገር ምንነት ተጠራጥሮ ሽፍኑን ግልጽ በማድረግ ሲያወድም ሁለተኛው ቅርፊቱ ወድሞ ዕርቃን የቀረውን አይናችንን ከፍተን በማጤን ትክክለኛ ግንዛቤ አዳብረን ነገሩን ዳግም ገንብተን ተንሳኤውን እንድናምን ይሆናል፡፡ ይህ በምልክቱ ግንዛቤ እና በግለ-ግንዛቤ መሃከል ሥነ-ትርጉም በመስጠት ለማቆራኘት ትርጓሜውን አስመልክቶ በመዋቅራዊ ገለፃ መተንተን ግጨቱን አስወግዶ ተቃርኖውን በማቆራኘት ስምም ሆነው ማለትም ነጩና ጥቁሩአንድ እና ተደጋጋፊ ይሆናሉ፤ «በተዋህዶ ይከብራሉ»፡፡ የተቀናቃኞች መቆራኘት ተቃርኖአዊን ግንኙነት በእርቀ ሰላም ይቋጨዋል፡፡ይህ ሂደታዊ የተቃራኖ እርቅ አካሉን በሙሉ ህልውናው እንዲኖር በማድረግ ከራሱ ሳይነጠል «ከቃል-ኪዳን ምድር» ያደርሰዋል (ኢታዎ፣ 2010፣ 10-13)፡፡

> *More than anything, dialectics is the culmination of reflection and the hermeneutics of symbols. So here after passing through a rigors test of suspicion and the penetrating gaze of faith, the subject who was dispossessed and reinstated, put to death and restored to life, now finally stands with hope at the threshold of the promised land of ontology where he shall be at home again, no longer alienated from himself* (Itao, 2010:13).

አለው፡፡ ለኮህን (ካፍሌይ፣2011፡ 191 እንዳመላከተው) ሥነ-ዘዴው አስገዳጅ የሆኑ ቅድመ-ተከተላዊ ክውኖችን እና ሥነ-ዘዴ ላይ የተጣበቀ (avoides method for method's sake)ሳይሆን በተዛምዶአዊ ትስስር ውስጥ ተከታታይ ለውጦችን በሚፈጥሩ ሥድሰት መሰረታዊ መመሪያዎች የታጠረ ነው፡፡እነሱም

1. *ሥር ለሰደደው ፍላጎት መታምን ወይም ለጥናቱ አላማ እና ግብ ቅድሚያ መስጠት፣*
2. *ለጥናቱ ዋና አጠይቆት ምላሽ ለመስጠት መነሳሳት፣*
3. *ተሞክሮዎቹን እንደ ተኖረው ለመከሰት መጣር፣*
4. *የተከሰተውንጉዳይ/ ነገር በጽሁፍ መግለፅ፣*
5. *በጽሁፍ የተከሰተውን በማጤን መላልሶ መፃፍ እና*
6. *በጽሁፍ የተዘረዘሩትን ክፍሎች እና ሙሉውን መመልከት ናቸው፡፡*

ሥነ-ዘዴው የሚካሄደው እኝህ ተያያዥነት ያላቸውን አንኳር ነጥቦችን የዳበረ ገላጭ ቋንቋን በመጠቀምእጅግጥልቅ እና ድርብርብ ምልከታ (layered reflection)ታግዞ ነው፡፡ ይህ የሚከወነው የአካሉን ተሞክሮ በመለየት እና የተሞክሮውን ትርጉም በተሻለ ጥልቀት መረዳት ስለሚቻል ነው (ሰሚዝ 1997፣ በካፍሌይ 2011፡ 191 የተጠቀሰ)፡፡

ዊልሰን እና ሃቺንሰን (1991) እንዳስረዱት ለትርጉም ተለይተው የሚዘጋጁት ጉዳይዎችም በተሞክሮ ውስጥ የመጡ ቁም-ነገር አልባ እና አላስፈላጊ ከሚመስሉ ገለፃዎች ሲሆኑ የሥነ-ዘዴው አትኩሮትም በሂደቱ እውነታን በማፍለቅ ትርጉም ፈጥሮ ጉዳዩን ማስረዳት ይሆናል (በካፍሌይ 2011 ፡ 191 የተጠቀሰ)፡፡አንደ ሻርኬ ምልከታ (ካፍሌይ 2011፡ 192) በዚህ ሂደት የተካሄደ ጥናት ግብ ቴክስቱን አንባቢው ሊረዳው የሚችለውን ወይም የተረዳውን ፍካሬአዊ ትርጉም መስጠት

ሳይሆን ከአንባቢው ግንዛቤ ውጭ በመጓዝ በቴክስቶቹ የተገለጹትን እና ዓይናችን ስር ያሉ ተሞክሮዎች አንባቢውን ወደ ቴክስቱ/ድርሰቱ በመጥራት ከሥነ-ጽሁፋዊው ዓለምእንዲገባ ማድረግ ይሆናል፡፡

ከለይ ከሰፈሩ ነጥቦች በመነሳት ያሁኑ ጥናት በተንታኝ ሥነ-ትርጉማዊ ክስተተአካል የጥናት ሥነ-ዘዴ ማእቀፍ ውስጥ ያርፋል፡፡ በዚህ ጥናት የክስተተአካልን ጽንሰ-ሃሳብ ባህሉ ከለመዳቸው ወዲህ ፍካሬልቦናንወዲህም ሃዲስ ታሪካዊነትንወዲህም ከሶሲዎሎጂ የትምህርት መስክ በቃረምኳቸው እሰቦች ተገልግያለሁ፡፡ ፍካሬልቡና በተመለከተ የሳይንሱ አባት የፍሮይድን እሰቦች ከግምት ውስጥ ባሰገባም፣ ጥናቴበዋናነት የላካን የፍካሬ ልቡና እስብ ላይ አተኩሬላሁ፡፡ ምክንያቴም የላካን የፍካሬልቡና እሳቤ «ቋንቋ» መሰረት በማድግ ማንነትን ከመህበረሰቡ ባህልና እምነት ጋር በማቆራኘት ለመበየን ያለመ በመሆኑ ለጥናቱ ግብ መምታት ጉልህ አስተዋጽዎ እንደሚኖረው ስለታመነበት ነው፡፡ በተጨማሪም የላካንን እሰብን ከክስተተአካል ጋር ለማቆራኘት የተመቻቸስለሆነ ነው፡፡ሃዲስ ታሪካዊነት ከማነሳው ታሪካዊ ከሆነው የአብዮቱ ዘመን ጋር በቀጥታ ስለሚገናኝእና ዘመኑ በገጸ-ባህሪያቱ ማንነት ላይ ያኖረውን ተጽእኖ ለማመላከትነው፤ (ላካን፣ በዚህ ረገድ የሚያስቀምጠው የሥነ-ጽሁፋዊ ሂስ አሰጣጥ ተረክ አለ፡፡) ጥናቱ በታሪክ ብቻ ሳይሆን በግለሰብ-ማህበረሰብ ተዛምዶም የተበየነ ነውና «ምጥን»የሶሲዎሎጂ እስቦችንም ከግምት ውስጥ ማስገባቱ አልቀረም፡፡

## 3. ክስተተአካላዊ የአብዮት ዘመን *ማህበረግለሰብ* ማንነት አመሳሰል በመረቅ

ከላይ የተመለከተውን ክስተተአካለዊ የጥናት አካሄድ በይነ-ዲስፕሊናዊነትን በተላበሰ መልኩ የማቀርበው በይነ-ቴክሰታዊ ሂስ (በሌሎች ታሪክ ቀመስ መፃህፍት ላይ ተመረኮዞ መረቅን የማ'የስ ውጥን) በሁለት ክፍሎች  የተዋቀረ ነው፡፡

### 3.1. ክስተተአካላዊ ማንነት ከማህበራዊ መነሻዎች አንፃር

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር በ«መረቅ»የመጡ ሁለት በጋር የሚያገለግሉ እምነት መር ትዕምርታዊ አስተማስሎዎች ተከስተው እናገኛለን፡፡ በመጀመሪያው የማመለከተው የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑትን ገጸ ባህሪያት ሲሆን ቀጥዬ የማመለከተው በማርክስ ርዕዮት አለም አምነው የሚመሩትን ይሆናል፡፡ ይህን «ክሰታ» በማስከተልም ሥነ-ትርጉማዊ ትንታኔ የማቀርብ ይሆናል፡፡

#### *3.1.1. ክስተት-አንድ፡ የኦርቶዶክስ ክርስትና*

ሮዛ የአላዛር እናት፣ ትደነቂያለሽ የተባራኪ እናት፣ታዚና የእዝራ አባት እና እዝራ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ የእምነታቸው ምስሶም በመጽሃፍ ቅዱስ የሚገኘው የእግዚሃብሄር ትዕዛዛዊ ቃል ነው፡፡ በመፅሃፍ ቅዱስ እንደሚነበበው የእግዚአብሄር ህግ ለሚያምኑበት የመንገድ መብራት ነው፡፡ ይህ መንገድም መድረሻው ከህይወት በኋላ በጽድቅ በገነት በዘላለማዊ ህይወት ህያው ሆኖ መኖር ነው፡፡ ለዚህም ጽድቅ ለመብቃት ለዕምነቱ ተከታዮች በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን እንደ ህግ የተቀመጡ መመሪያዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ህግጋቶች ሥነ-ምግባራዊ ናቸው፡፡ ምክንያቱም አታድርግ ወይም አድርግ በሚል የተቀነበቡ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሥነ-ምግባራዊ ህግጋቶች ውስጥ «አታመንዝር» አንዱ ነው፡፡ ነግር ግን ከላይ የተመለከቱት ሁሉም ከዚህ ሃይማኖታዊ የሥነ-ምግባር መመሪያ ይወጣሉ፡፡
ሮዛ ቤተ-ክርስቲያን አዘውትራ ተሳላሚ ነች፡፡ ሮዛ ባለትዳር፣ የአላዛር እናት ብትሆንም ከልጇ ጓደኛ ዲያቆን ከሆነው ከእዝራ ጋር በድብቅ ፍትወት ታደርጋለች፡፡ ይህንን እውነታ የሚነግረን በእዝራ ነው፡፡ እዝራም አብዝቶ በሮዛ ውበት ፍትወቱን ይወጣል፡፡ በመጽሃፍ ቅዱስ ያየ የተመኘ እንደ አመነዘረ በሃጢያት እነደወደቀ ነው የሚነግረን፡፡ በዚህ ከሄድን እዝራ ከእምነቱ እንዳልሆነ እንመለከታለን፡፡

የእዝራ አባትም በኦሮቶዶክስ የሚመሩ እና በሃይማኖታዊ ትምህርቱም ቄስ ቢሆኑም ቅሉ በተደጋጋሚ ከተለያዩ ኮረዳ ሴቶች፣ በትዳርም ካሉ ሴቶች ጋር በተመሳሳይ የማመንዘር ሃጢያትን መፈጸማቸውን ለልጃቸው ለእዝራ አጫወተውታል፡፡

ትደነቂያለሽ የተባራኪ እናት አዘውትራ ቤተ-ክርስቲያን የምታስቀድስ እንዲሁም የምትፆም ብትሆንም አቶ ከሚባሉ ሰውዬ ጋር በተደጋጋሚ አንሶላ መጋፈፏን እንረዳለን፡፡

ከእነዚህ ከሱት ድርጊያዎች የእምነቱ ተከታዮች በእምነታቸው ሥነ-ምግባር ውጭ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ማህበረሰቡ ከሚፈቀደው ውጭ በድብቅ የፍትወት ህይወትአላቸውና፡፡ ለምሳሌ፣ ቄስ ታዚና «በአትኮኝ የለሽ» ጥበብ እየታገዙ እራሳቸውን በተለያዩ ዘዴዎች ቄስነታቸውን ይደብቃሉ፣ ሮዛ ጨለማን ተግን በማድረግ፣ አላዛር ጉዳዩን ለራሱ ብቻ በማድረግ፣ ትደነቂያለሽ ከአከባቢው በአቶ መኪና በመሄድ ነው ይህን መጽሃፍ ቅዱሳዊ እምነት የሚጥሱት፡፡

በድርሰቱ የአንድ አከባቢ ነዋሪዎች እና ጎረቤታሞች የሆኑት ገጸ-ባህሪያት የሚለዩዋቸው ነባራዊ ጭብጦች እንዳሉ ሆነው (ለምሳሌ፣ የትምህርት ደራጃና ስራ እንዲሁም የሃብት ደረጃና የኋላ ታሪክ) በማህበራዊ ህይወታቸው ትስስር ምክንያት አንዳቸውን ከሌላቸው ለይተን መመልከት ይከብደናል፡፡ በዚህ ረገድ እምነት በዋናነት የጋራ የሚሉትን ማህበራዊ እሴት ይሰጣቸዋል፡፡ በሌላ በኩልየተመለከትነው ማህበራዊ አንድነታቸውን ባፋለሰ መልኩ ከዕመነታቸው አንፃር ኢ-ሥነምግባራዊ ከህገ-ሃይማኖት መተላለፍ አንድ መሆናቸውን ያረጋግጥልናል፡፡ የዚህ ክስተት ትንታኔ ክስተት ሁለትን ተከትሎ ቀርቧል፡፡

### *3.1.2. ክስተተሁለት፡ ማርክስ*

በክስተተ ሁለት በማርክስ ርዕዮተ አለም የሚያምኑትን እንመለከታለን፡፡ በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ከመግባታችን በፊትድርሰቱ የተተከለበትን የዘመን መንፈስ ማሳየት ቀጠሎ ለሚመጣው ክስተተአካላዊ ትንታኔ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ይህን የዘመን መንፈስ በተዋረድ እና በአግድሞሽ (Verticaly and Horizontaly) ለማየት እንሞክር፡፡በተዋረድ (Verticaly)ዘመኑን ስንቃኘው ኢትዮጵያ ከላይ ወደ ታች በሚወርደው የማዕከላዊ አስተዳደር የሶሻሊዝም ርእዮተ አለምን የተከተለችበት እና በዚህ ሂደትም ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ የሆኑ መንግስታዊ የለውጥ እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደረገችበት ነው፡፡ እነዚህም በዋናነት በአዋጅ ከላይ ወደ ታች ወርደው የተከናወኑ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የገጠር መሬት አዋጅ፣ የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤት አዋጅ፣ ትምህርት ለማስፋፋት የእድገት በህብረት ዘመቻ፣ እና እስከ ግድያ የዘለቀ የነፃ እርምጃ ማለት የቀይ ሽብር አዋጅ ወዘተ፡፡በአጭሩ እነዚህ በማእከላዊ መንግስቱ የተወሰዱት እርምጃዎች ተፈፃሚነታቸውን ያገኙት ርዕዮተ አለማዊ ግንዘቤን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

ዘመኑን በአግድሞሽ(Horizontaly) ስንመለከተው በሃገራችን ተበታትነው የሚገኙትን ያልተማሩ እና የተማሩ (ማንበብ እና መፃፍ የሚችሉ እና የማይችሉትን) የህብረተሰብ ክፍሎችን እናገኛለን፡፡ በዚህ ረገድ ዘመናዊ ትምህርት የተከታተሉ ማህበራዊ ግልሰቦች (ሲቪል) የወታደሩን አብዮትእና ስልጣን በመቃወም በመላው ኢትዮጵያ እና በውጭ ሃገራት መጠነ ሰፊ የሆነ እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡ በተለይም የተማረው እና ከተሜ የሆነው የማህበረሰብ ክፍል እራሱን በተለያዩ ፓርቲዎች በማደራጀት የወታደሩን አብዮት/ ወታደራዊ ስርአት ለመፈታትን ሞክሯል፡፡በዚህ መሰረት አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ግን ለመጤው ርዕዮተ አለም እንግዳ መሆኑን ሳንዘነጋ ከላይ ወደ ታች እና ከጎን ወደ ግራ የዘመኑ መንፈስ በሶሻሊዝም የታጠነ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህ በርዕዮተ አለም አንድ መሆን ወይም ያለመለያየት ሶሻሊዝም በዘመኑ ምን ያህል ይታመንበት እንደነበር አመላካች ነው፡፡ በሌላ አነጋገር እንዚህን አካላት አንድ የሚያድራጋቸው ጉዳይ ቢኖር የማርክስ እና ሌኒን የፍልስፍና ርዕዮተ አለም እሳቤን እንደ ችግር ማስወገጃ፣ እንደ እድገት እና ብልፅግና መሸጋገሪያ እና እንደ ምህረት ማፍለቂያ እድርገው መውሰዳቸው ነው፡፡

ይህ በታሪክ የተከሰተ ጉዳይ በቀጥታ መንገድ ሁለቱ ተቀናቃኝ የማህበረሰብ ክፍሎች አብዮታቸውን ያካሄዱት የማርክስ-ሌኒን የፖለቲካ-ኢኮኖሚ ፍልስፍና እንደ እምነት በመቀበል እና በማመን ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ ይህን ሃሳብ በሁለት መረጃዎች ለማጠናከር እሞክራለው፡፡ የመጀመሪው ርዕዮተ አለሙ የተሰራጨበትን ሂደት ልክ እምነት በተስፋፋበት የሰበካ ስልት መሆኑ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የተካሄደውን አብዮት አስመልክተው ሰፊ ሃተታ ያቀረቡት የፍልስፍና ባለሙያው መሳይ ከበደ እንደሚከተለው ጽፏል፡፡

> *Though the revolution undertook a systematic attack against the church and distinguished itself by the attempt to spread irreligion, it acted as anew religion by harboring, beyond the need to correct the existing system, the goal of regeneration of the human race. This redemptive objective explains why like religion, the revolution spread through preaching and propaganda; it also explains why it adopted a universal and abstract language and activated powerful and violent emotions. (Mesay, 63-64)*

ሁለተኛው ማስረጃዬ ርዕዮተ አለሙ በግለሰብ ደረጃ እንደ እምነት የአምልኮ ቦታን መያዙ ነው፡፡ ማርክሲዝም በሃገሪቱ የሰፈነውን ኢፍትሃዊት ገላጭ እና ብቸኛ መፍተሄ ሆኖ መወሰዱ ርዕዮተ አለሙን ተመራጭ ሳይሆን ተመላኪ ሆኖ እንዲወጣ አድርጎታል፡፡ ይህም እምነቱን የማይጠየቅ አድርጎታል፡፡ ስለዚህም ግለሰቡ እንዲቀበለው የተገደደበት ዘመን ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በዘመኑ ካለፈቸው ሕይወት ተፈራ ተሞክሮ እንይ፡፡

> *Marxism had become my religion. I was baptized by those poetic words in The Communist Manifesto, the Economic and Philosophic Manuscripts of 1884, Theses on Feuerbach and the Holy family. Marxism opened my eyes to the injustice around me and inspired me to fight and destroy the oppersive and exploitative system and built a better one on its ashes. I did not look out my own salvation but wanted to live and die for the liberation of the masses. (Hiowt, 2012:158)*

የዘመኑ መንፍስ የማርክስ ርዕዮተ አለማዊ ፍልስፍና እንደ እምነት የተመለከተበት እንደነበር እነዚህ ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ ርዕዮተ አለማዊ እምነት ሥነ-ምግባር ስናወጣ የምናገኘው ዋና መመሪያ ለማህበራዊ እኩልነት ትግል ውስጥ መታገል ይሆናል፡፡ ትግሉ የተካሄደው አንድም ርዕዮተ አለሙን በመቀበል፣ በመደገፍ እና አባላትን በመመልመል አንድም ርዕዮተ አለማዊ መፍከሮችን በማንገብ ማእከላዊ መንግስትን በተላያዩ ስልቶች በመቃወም እና በመደገፍ ነበር፡፡ ማእከላዊ መንግስትን መቃወሚያ ስልቶች የሆኑት በራሪ ወረቀቶችን በመበተን፣ ፖስተሮችን በመለጠፍ፣ ሰላማዊ ሰልፍ በመወጣት እንዲሁም ከመንግስታዊ መመሪያዎች እራስን በማግለል ነው፡፡ከእነዚህ ውጭ በውይይት የሃሳብ ልዩነቶችን በንግግር መፍታት የወቅቱ ትግል መገለጫ አልሆነም፡፡ ሌላው ቀርቶ ውይይት የመአከላዊው መንግስት ተቀኛቃኝ ፓርቲ በነበሩት ኢህአፓ እና መኢሶን መካከል እንኳ አልነበረም (መረራ፣ 68፣ 2005)፡፡ በአጭሩ ሃሳብን በሃሳብ የማሻነፊያ እንዲሁም የማሻሻያ መንገድ አልተገነባም፡፡ ይህም በዘመኑ ትግል ውስጥ አላማን ማሳካት እንጂ ሃሳብን ማወዳደር አልተካሄደም፡፡ ይልቁን በሁሉም በኩል በኩል ልዩነቶችን በጠመንጃ ለመፍታት ተሞክሮዋል፡፡ የዚህ ውጤቱ ደግሞ ምንም ሳይሆን መጠፋፋት እና ሃጋራዊ ክስረት ብቻ ሆኖ አልፏል፡፡

መንግስት በበኩሉ በዋናነት የ«ፍየል ወጠጤ» መግለጫ በመገናኛ ብዙሃን በማቅረብ የገደላቸውን ተቀናቃኝ ግለሰቦች በማሳወቅ «አብዮቱ»ን ለመምራት ሞክሯል፡፡ መግደልን ጨምሮ እነዚህ የትግል ስልቶች የማርክስ እምነት ተከታዮች ሥነ-ምግባራዊ መመሪያዎች ሲሆኑ ከእነዚህ ውጭ መሆን በዘመኑ ከባድ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ከመንግስት ወገን በመሆን አብዮቱን የመሩት ደበላ ዲነሳ በዘመኑ ሶሻሊዝም ፋሽን እንደነበር ጠቁመዋል፡፡ እንደ ደበላ ግንዛቤ ዕርዮት አለሙ በኢትዮጵያ እንደ ኦክስጅን የተማገ ሲሆን እውነታ በመላው አለም የተስተዋለ ነው(2006፣ 241)፡፡

በድርሰቱ ተባራኪ ከላይ በተጠቀሰው የዘመን መንፈስ ውስጥ ተውጣ የማርክሲም እምነትን ትከተላለች፡፡ የተባራኪ ውክልና ግን ለእራሷ ብቻ ሳይሆን ለእምነቱ ተከታዮች ሁሉ ነው፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደተመለከትነው ሃይማኖት ማህበራዊ እና ቡድናዊ አስተማስሎ በመሆኑ ተባራኪ የምትከተላቸው እና የሚከተሏት ስላሉ ነው፡፡ ይህ እምነት ለተባራኪ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ግላዊ ግንዛቤዎቿን የምትመለከትበት መነጽር ነው፡፡

> *በምድር ላይ ሌሎች ፍልስፍናዎች ቢኖሩም፣ ማርክሲዝምን ሊቋቋሙ የማይችሉ መሆኑ በደመ ነፍስ ገባኝ፡፡ እነዚህን የያዘ ሁኑን የያዘ ይመስላል፡፡ ፍቅር ምንድነው ለሚለው ጥያቄ ያገኙሁት ምልስ አጭር ነበር፡፡ በመደብ በተከፋፈለ ሕበረተሰብ፣ ለጥቅም በሚነታረኩበት አለም ላይ፣ በስስትና በስግብግብነት ጦርነት የሚወጡ ህዝቦች ፍቅርን ሊያውቁ አይቻላቸውም፡፡ ፍቅር ትክክል የሚሆነው በሶሻሊዝም ነው፡፡ ማርክስ ፈረንጅ ሳይሆን የእዝራን አባት መሰለኝ…፡፡ ጎረቤቴ ወዳጄ ሳጠፋ ቀርቦ እጄን ይዞ የሚመክረኝ፣ የሚያበረታታኝ፣ ሲጨልምብኝ ይሄው መንግዱ የሚለኝ፡፡ ለእኔ፣ ለደሃና ለሃገሬ ያሰበ፡፡ በመጠኑ የእኔ ስንፍና ቢኖርበትም ቤተክርስቲያንን ናቅሁ፡፡ ቄስና ፓስተር የህልም ቸርቻሪዎች ሆኑብኝ፡፡ ነፃነትን ከሰማይ አልጠብቅም፡፡ ነፃነት ዝናብ አይደለም፡፡ ነፃነት በትግል ነው፡፡ በሆያ ሆዬ እንደ ጢቢኛ አይገኝም፡፡ አዲስ ሰው ሆንኩ፡፡*

ከላይ እነደተመለከትነው ተባራኪ ሙሉ በሙሉ የርዕዮተ አለሙ ተከታይ ብቻ ሳትሆን እንደ እምነት የተቀበለች ሆናለች፡፡ ማርክስን በቄስ መመሰሏ እና የጨለማ መሪዋ ማድረጓ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ናቸው፡፡ በእምነቷም የትግል መንፈስን ሰንቃ ተንቀሳቅሳለች፡፡ ከላይ በተገለጸው መሰረት ተባራኪ ከሌሎች የትግል አጋሮች ጋር በመሆን መንግስትን በሚቃወሙ ሰልፎች ላይ ተሳትፋለች፣ በህቡእ የተለያዩ ውይይቶች ውስጥ ገብታለች፣ አባል ለመመልመል ተንቀሳቅሳለች፣ እንዲሁም የጨለማ ተቃውሞ ውስጥ ተሳትፋለች፡፡ ከትግል ውጭ ያሉ ጉዳዮች ለተባራኪ አላስፈላጊ እና ጥቅም የለሽ ሳይሆኑ እርኩሰት ወይም ሃጢያት አድርጋ ትወስዳቸዋለች፡፡ ለምሳሌ በተደጋጋሚ እንደታየው ከአብሮ አደግ ጓደኛዋ እና የፍቅር ግንኙነት ከነበራት ከአላዛር ጋር የነበራትን ከጫወታ እስከ ድሪያ የዘለቀ ግንኙነት አቁማለች፡፡ ይህ ግንኙነት የቆመው በዋናነት አላዛር የእሷ እምነት አራማጅ ባለመሆኑም ጭምር ነው፡፡ እንደ እሷ እራሱን ወደ ትግሉ ጎራ ስላልቀላቀለ፡፡ እንዲሁም በእምነቷ ታግዛ የአከባቢዋን ሰዎች ፈርጃ የግሏን ግንዘቤ ትይዛለች፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳይን ተባራኪ ማረክሲዝምን እምነቷ ማድረጓ ነው፡፡ እዚህ ጋር በክፍል አንድ ክስተተ ውስጥ የተመለከተውን ነገሮችን በፅድቅና በኩነኔ ወይም በዕርኩሰት ማስቀመጥ የዕመነት መገለጫ ባሕሪ ማስታወስ የስፈልጋል፡፡ በሌላ አነጋገር የራስን አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ ሃሳብና ድርጊት አይነኬ በማድረግ ለሌላው ማራከስ እምነትን ያረጋግጣል፡፡ እምነት ደግሞ አይፈተነም፡፡

ባጠቃላይ ተባረኪ እንደ እምነቷ ታግላ ፅድቅ የምትለውን የእምነቷን ቱሩፋት ለመቀዳጅት በትሞክርም በተደጋጋሚ እንደምንመለከታት ይህን እመነቷን ከእናቷ ማስቀደም እና ከምታፈቅረው አላዛር መነጠል ተስኗታል፡፡ ይህም ከማህበሯ የትግል ሥነ-ምግባር ውጭ ያደርጋታል፡፡ በአንድ በኩል የእናቷ ፍቅር በሌላ በኩል የወንድ ጓደኛዋ ፍቅር ከእምሮዋ በላይ እየሆነ እምነቷን እጅጉን ሢፈታተናት እንመለከታል፡፡ ይህን ክስተተ ከስነልቦና አንፃር ተምልክተን በሰፊው እንመለከተዋለን፡፡

### *3.1.3. የክስተተ አንድ እና ሁለት ሥነ-ትርጉማዊ ትንታኔ*

ማህበረሰብ የግለሰቡ መገኛ እና ግለሰቡ የማህበረሰብ መስራች በመሆኑ በሁለቱ መሃከል የነብስና የስጋ ያህል ቁርኝት እንዳለ የአንትሮፖሎጂ እና ሶሲዎሎጂ የጥናት መስክ ተመራማሪዎች ቢያመላክቱም፤ ግለሰብ ማህበረሰብ፣ ማህበረሰብ ግለሰብ ነው የሚል መደምደሚያ ግን ከማቅረብ ይቆጠባሉ፡፡ ከዚህ ይልቅ ባለሞያዎቹ ለሁለቱም የየግል መገለጫዎችን አቅርበው ማህበረሰብ እጅጉን በጋራ የቡድን አስተማስሎዎች (collective representations) የተዋቀረ በመሆኑ

አብዝቶ ሐይማኖት/እምነት ማህበረሰባዊ መገለጫነቱ ይጎላል[5]፡፡ ሃይማኖታዊ አስተማስሎዎች የጋራ እውነታ መገለጫ ቢሆንም ይህ ለግለሰቡ መገለጫ ሆኖ አያገለግልም፡፡ በሌላ አቀራረብ እምነት ማህበራዊ ቢሆንም የግል ነው፡፡ ለምሣሌ፣ እያንዳንዱ ግለሰብ የማህበረሰብ አባል ስለሆነ ብቻ በግዴታ ተስማምቶ የእምነት ተከታይ መሆን አይጠበቅበትም፡፡ በሌላ አረዳድ፣ ለሥነ-ሰብ ተመራማሪው የግለሰብ አፈንጋጭነት የማህበረሰብ አንዱ መገለጫ ወይም ባህሪይ ነው፡፡ ሃይማኖት ቅዱስ እና አይነኬ በሆኑ አስተማስሎዎች የተመሰረተ በመሆኑ ለሌሎች ማህበራዊ አስማስሎዎች ምንጭ ሊሆነን ይችላል፡፡ ከእነዚህ አይነኬ፣ አይታሰቤ ወይም አይደረሴ ሃይማኖት መር አስተማስሎዎች ውስጥ ማህበራዊ የሆነውን *ሥነ-ምግባር* ማፍለቅ ይቻላል፡፡ እንደ ሃይማኖት ሁሉ ሥነ-ምግባር ግንባታው ማህበራዊ (Socially Constructed) ነው፡፡ በእርግጥ የተቀደሰ/የተኮነነ፣ የተፈቀደ/ የተከለከለ፣ ትክክል/ ስህተት ወ.ዘ.ተ ባጠቃላይ ሥነ-ምግባራዊ/ ኢ-ሥነምግባራዊ በራሱ የሆነ ነገር ባይኖርም ማህበረሰቡ በጋራ እንደሆነ አድርጎ አበጅቷቸዋል፡፡ [What makes religion distinctive is its focus on the sacred, which itself is a social construction. There is nothing inherently sacred or profane in the world. A place, a symbol, a personality becomes sacred because it's socially constructed. Moore, 2009:57]

ይህን መሰረት ባደረገ መልኩ፣ በክፍል አንድ የተመለከተው ከስተታዊ እውነታ የሚያስረዳን ከዕምነት ህግ መራቃቸው በእምነታቸው ምቾት እንደማይሰማቸው፣ እምነታቸው ነፃነታቸውን እንደነፈጋቸው፣ እምነታቸው (ተፈጥሮአዊ) ፍላጎታቸውን እንደጨፈለቀባቸው ነው፡፡ ሌላው መሰረታዊ ነጥብ፣ ይህን እምነታዊ ምቾት ማጣትን በግልፅ መነጋገር አለመቻላቸውና ኢ-ሥነምግባራዊ መተላለፋቸውን በድብቅና በከለላ እውን ማድረጋቸው ነው፡፡ የዚህን ምክንያት በሶሻል-አንትሮፖሎጂ የሃይማኖት ትንታኔ ስንመዝነው ለጉዳያችን አብሪ ጥይት ይሆነናል፡፡ እነዚህ ሳይንሶች እምነት በአይነኬ አስተማስሎዎች የተቀነበበ ፅነሰ-ሃሳብ በመሆኑ ለውይይትና ለመሻሻል ክፍት እንዳልሆነ ያስረዳሉና፡፡ ይህ የእምነት መርህለፍላጎቶች መታጎል ስነልቦናዊ ጫናው የጎላ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ የዚህ የታፈነ ማህበረሰብ ፍሬ የሆኑት ገጸ-ባህሪያት(አላዛር፣ ተባረኪ፣ እዝራና ማከዳ) በሚቀጥለው ክፍል ተዳሰዋል፡፡

ከላይ በክስተት ሁለት ተከስቶ የተመለከትነው የተባራኪ ከምትከተለው እምነት በመውጣት ወደ ምትፈልገው አንድም ወደ ትደነቂያለሽ እናቷ ወይም ወደ አላዛር የልብ ወዳጇ አለመመለሷ እንደ ክሰተት አንድ ሁሉ ምን ያህል እምነቷ የታፈነ እንደነበር አመላካች ነው፡፡ ይህም ሲባል ተባራኪ ምርጫ የሌላት ነበረች፡፡ ምረጫዋን እውን ከመድረግ የሚያግዳት የምትከተለው እምነት ነው፡፡ ይህ በስነ-ልቦናለዋ ላይ መታጎል መፍጠሩ አይቀሬ ነው፡፡ በጉዳዩ ዙሪያ እውነታውን ወይም ምልከታዋን ከማንም ጋር አለመነጋገሯ የእምነቱ አራማጅ የሆኑት የማህበረሰብ ክፍሎች በዕምነታቸው ዝግ ወይም ለሃሳብ ልውውጥ ክፍት አለመሆናቸውን ያስረዳል፡፡

ይህ አይነኬ በሆነው እምነት ሰበብ የታጠረውና የታፈነው ማህበረሰብ ከሶሲዎሎጂ ሳይንስ አንፃር ጤናማነትን እንደማያላብስ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ <u>ምንም እንኳን እነዚህን ሳይንሶች ባልጎለብትባቸውም</u> ከመጠነኛ ዳሰሳዬ እንደተረዳሁት ለዋናዎች እና ለመጀመሪዎቹ የሰይንሱ አባቶች (ለማርክስ፣ ለደርክሄም፣ ለማክስ ሜበር፣ እነዲሁም ለፍሮይድ) እምነት ማህበረዊነቱን ጨርሾ ባያጣም ነፃ-አቋማት (ሴኪውላር) ለምሳሌ እስፖርት መህበራዊ መስተሳሰር እንደሚፍጥሩ ነው የሚተነትኑት [(ኢማ ቶማሊን፣ 2007 2-7)፡፡ the declining of religious authority allowed the development of functional rationality]በተለይም ለደርክሄምና ዌበር ዝግ የሆነው ማህበረስብ ማመንን ገሸሽ

[5]ይህ ጉዳይ ለጥናቱ ግብ መሳካት ከሶሻልአንትሮፖሎጂ የጥናት መስክ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ፈጣሪዎች መሃከል ከደርክሄም የተነጠቀ ነው፡፡ "Religion is eminently social. Religious representations which express collective realities; the rite are a manner of acting which take rise in the midst of assembled groups and which are destined to excite, maintain or recreate certain mental state in these group." "A religion is totally a unified system of beliefs and practices related to sacred things, that is to say things set a part and forbidden- belief and practices which unite into one single moral community, called a church, all these who adhere to them." (Emile Durkheim, 1968 cited in Moore, D 2009: 56-57)

ማድረጉ ምክንያታዊ ያደርገዋል፤ ለተሻለ ሃሳብ የሚደራደርና በምክንያት ውጤት ያምናል የሚል ሲሆን ይህን ወደ ሃገራችን ብንመልሰው ወደ ልቦለዱም ብናማትር አናገኘውም፡፡ በድርሰቱ ማህበራዊው መታፈን ከሳይንስምከእምነትም አለመሆን አስከትሏል ማለት ይቻላል፡፡  ይህም ማህበረሰቡ ባካና መሆኑን ያሣያል፡፡ በአጭሩ፣ የተመለከተው ማህበረሰብ ጤናማ አይደለም፡፡

በክፍል አንድ ድርሰት እጅጉን ማህበረ-ባህላዊ ምርት መሆኑን ከግምት በመከተት፣ የአብዮት ዘመን *ማህበረሰብ* ማንነት አመሳሰልን ‹‹መረቅ›› የተባለውን የአዳም ረታ ልቦለድ ጠርቶ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ እንደተከታተላችሁት ‹ማንነት›ን ከሥነ-ህይወታዊ እና ከፖለቲካዊ (የብሄር ፖለቲካ ልብ ይሉዋል) አንድመታው ለማውጣት እና ህያው የባህል አውድ ውስጥ ለመጨመር ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህም የግድ አስፈላጊ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ በመቀጠል በ‹‹መረቅ›› እንዴት ማንነትን ማህበራዊ ከሆኑተ የዕምነት እና የማርክስ እሳቤዎች አንጻር ታሪካዊ ዳራውን ከግምት በማስገባት መፈተሽ እንደሚቻል አይተናል፡፡  በመጨረሻም ለቀረበው ኹነት አንድምታ/ ትርጓሜ ለማቅረብ ጥረት ተደረጓል፡፡ አዳም ረታ ባለብዙ ርዝቅ ደራሲ ከመሆኑም በላይ ሌላ ብዙ ሊነገርለት የተገባ ቁምነገሮች አሉት፡፡ በአገራችን የሥነ-ጽሁፍ ካርታ ላይ ጉልህ አሻራ እያኖረ የሚገኘውን ይሄን ሰው አንስተን እንድንነጋገር እወዳለው፡፡  በዚህ አምድ የግለሰብን ሥነ-ልቦና አወቃቀር ለመፈተሽ እንሞክራለን፡፡

## 4. ክስተተአካላዊ ማንነት ከስነ-ልቦና መነሻዎች አንፃር

> *If psychoanalysis can help us better understand human behaviour, (and) then it must certainly be able to help us understand literary texts, which are about human behavire.*
>
> **-Tyson, Lious 2006፡11**

ከላይ እንዳመለከትኩት በሁለቱም የዕምነት ረድፍ የተሰለፉት በድርሰቱ የመጡ ገጸ-ባህሪያት ከማህበራቸውየዕምነት ስነ-ምግባራዊ ሕግ ማፈንገጣቸውን ነው፡፡ ይህ ፍንገጣ መነሻው እምነት በአይነኬ አስተማስሎ ከመገንባቱ የተነሳ እንደተከሰተተመልክተናል፡፡ የማህበረሰብ በዕምነት የተመራው መታፈን ወደ ውይይት የሚያመራውን ጎዳን ዝግ በማድረጉ የተነሳ ማህበረሰቡ የጤናማነት ተምሳሌት ሊሆን እንደማይችል ገምግመናል፡፡ የዕምነት አይነኬ መሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት እንዳይፈጠር በማድረግ ለማህበራዊ ቀውስነት እንደሚዳርግ አይተናል፡፡ በዚህ ክፍልበድርሰቱ የተመለከቱትን ገጸ-ባህሪያትሥነ-ልቦናዊ ግንባት በክስተተአካላዊ የማንነትትንተና ቀርቧል፡፡ ይህን ማድረጋችን ሁለት ጉዳዮችን ታላሚ በማድረግ ሲሆን የመጀመሪያው በግለሰብ ደረጃ ያለውን ሥነ-ልቦናዊ የጤናማናት ሁኔታ ለማውጣት እና በሁለተኛነትም ከግለሰባዊው ስነ-ልቦናዊ ትንተና የጋራ የሆነ መገለጫ/ የተመሳስሎ ነጥብ ለማፍለቅ እንዲረዳን በማሰብ ነው፡፡ከሥነ-ልቦና መነሻዎች አንፃር የተደረገው የዚህ ክፍል ትንታኔ የላካንን የፍካሬ-ልቦና አረዳድ ከግንዛቤ በማስገባት የተከወነም ነው፡፡

*ሥነ-ፅሁፍና ሥነ-ልቦና* ከዘመነ አርስቶትል የሚነሳ የተራዘመ ግንኙነት ቢኖራቸውም በሥነ-ልቦና መነጽር ሥነ-ፅሁፍን ማየስ በሃኛው ክፍለ-ዘመን በፍሮይድ አማካኝነት እንደጎለበተ ይታመናል[6] (ሐቢብ፣ 2005 ፡571)፡፡ ፍሮይድ በቆረቆረው መንገድ ብዙዎች ቢራመዱም ፍሮይድን በጥልቀት በማጥናት የተለየ መንገድ ማፍለቅ የቻለው ፈረንሳያዊ ጃኪዩዝ ላካን ለዘረፉ ተጠቃሽ አስተዋፅዎ አለው፡፡ እንደ ፍሮይድ የላካን የስነ-ልቦና መዋቀር የተቀነበበው በሶስት

---

[6]ያልተሄደበት የፍሮይድ አስብ ማጠንጠኛው ሰው እራሱን እየተቆጣጠረ የሚመራው በንቁ የአእይምሮ ክፍል ሳይሆን ባሸለበው በኢ-ንቁ የአእምሮ ክፍል ነው የሚለው ነው፡፡ በዚህ ግንዛቤ መሰረትም ላራሳችን ጭምር ባዳ ነን፡፡ ኢ-ንቁ የሆነውን የአእምሮ ክፍል ለሳይንሳዊ የጥናት ሥነ-ዘዴ ክፍት እንዲሆን ማድረጉና ሥነ-ዘዴውን ለመተግበር የሚውሉ ቋንቋና ቃላትን መፍጠሩ ፍሮይድ ለዘረፉ ያበረከታቸው ሁለት መሰረታዊ ነጥቦች ሲሆኑ (በፍሮይዳዊያን ሶስቱ የሰብዕና መዋቅሮች Id, Egoና Superego ሲሆን፣በመዋቅሮቹ ውስጥ የሚፈልቁ ክስተቶች በሚያካሂዱት ፍትጊያ የግለሰቡ ማንነት ይፈጠራል፡፡) ይህም ለተራዘመ ዘመናት ይታመንበት የነበረውን የሰው ልጅ በሃልዮት የመመራት ዝንባሌ በእጅጉ የፈተነ ነው (ቴዎድሮስ 2005 ዓ.ም፣ ሐቢብ፣ 517)፡፡

ምሰሶዎች[7] ቢሆንም በላካን ግንዛቤ መሰረት ሰው የሚተዳደረው «ቋንቋ»ን መጠቀም በጀመርን ማግስት በምንገነባው ኢ-ንቁ የአእምሮ ክፍል ነው፡፡ በዚህ ግንዛቤ መሰርት ቋንቋ መቻል ትዕምርታዊ ወደ ሆነው ባህልን ማወቅንና ትረጉም መስጠት ወደ ሚጀመርበት አለም ያሸጋግረናል፡፡ ግልፅ ለማድረግ፣ ቋንቋ ማንነት የሚፈጠርበት፣ የሚታነጽበትና የሚበለጽግበትነው፡፡

በግለሰብ-ማህበረሰብ ቁርኝት የሚገናባው ማንነትያለቋንቋ አይታሰበም፡፡ ምክንያቱም በቅድመ-ቋንቋ ጨቅላው እራሱን መለየት አይችልም፤ ይልቁን ፍጹም እርሱነቱንና አከባቢውን ማገናዘብ ባልቻለበትና እራሱን በእናቱ የመሰለባቸውን ደረጃዎች አልፏል፡፡ ቋንቋ በፊት ካዳበረው ግንዛቤ በተቃራኒ ትርጉም ሰጥቶት እራሱን የተነጠለ ሆኖ ማንነቱን ያገኘዋል፡፡ ይህን መሰረታዊ የቋንቋ ስፍራ ሐቢብ ሲገልጽ፤ «It is not the subject who gives rise to language or who controls it; rather, it is language which governs and constitutes the subject... It is language, then, which determines and authorizes the range of cultural structures and possible experiences. >> (2005:594)ይላል፡፡ ሰው በቋንቋ ባህሉንና የማህበረሰቡን የግንባታ ምሰሶዎች ያውቃል፡፡ በእነዚህ እውቀቶቹም እየተመራ ፍላጎቶቹን ይጨፈልቃል፡፡ ይህም የስሜት መጨቆን ውጤት ይሆናል፣ ቋንቋ በራሱ ማጣት ነው፡፡

ይህ ላካን መር እሳቤ ቋንቋ ተኮር ስለሆነ ከሥነ-ትርጉማዊ ክስተተአካል ጋር ይዛመዳል፡፡ እንደ ኢታዎ (Itao) የሪኮር ሥነ-ትርጉማዊ ትንታኔ የሚያርፈው ባንድም በሌላም መንገድ «ቋንቋ» ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ቋንቋ «የሰው ልጅ» ማንነት መበየኛ ፣ ቋንቋ ሰው እሱነቱን የሚያገናዝብበት ጎዳና ስለሆነ (route of self understanding) እና ቋንቋ በባህሪው የአሻሚ ስለሆነ ነው፡፡ ይህም ባንድ ባኩል ሰው ሥነ-ልሳናዊ ማለት በቋንቋ እሱነቱን እና ከሌሎች አካላትና ከሚኖርነበት አላም ጋር ያለውን ዝምድና የሚያፀናበት ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቋንቋ ውስብስነት ስላለበት ነው፡፡ ቋንቋ ውስብስብ ነው ሲባል ከምልክትነቱ (sign) ባለፍ ትዕምርታዊ (symbolic) ማለትም የእማሬያዊ (patent meanings) እና የፍካሬያዊ (latent meanings) ብያኔዎች ተሸካሚ ስለሚሆን ነው፡፡ በዚህ ወቀት ከግልጹ ወደ ተሸሸገው ብያኔ ለመሄድ በተገለጸው ላይ ተመስርተን ሃሳባዊ ትርጓሜ መስጠት የግድ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ባንዴ እና ወዲያው ሳይሆን በዘገመ አስተውሎት የሚፈጸም ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሐይዲጋርን በመከተል ሪኮር ሥነ-ትርጉም ቋንቋን በምልዐት ሳይሆን ትዕምርታዊ የሆኑ ምልክቶችን ታሳቢና ተተኳሪ በማድረግ የሚካሄድ ነው የሚለውን ነጥብ አስቀምጧል (ኢታዎ፣ 2010፣ 2-5)፡፡

የሪኮር ሃሳብ ወደ ላካን ሶስተኛ ማጠንጠኛ እንድናልፍ የተመቸ ነው፡፡ በዚህ «እውነተኛ» በተሰኘው እሳቤ ውስጥ የምናገኘው ትርጉም መስጠትና ልንረዳቸው የማንችላቸውን ጉዳዮች ይመለከታል፡፡ እነዚህን አይደረሴ ጉዳዮችን ለመድረስ የግድ ርዕዮተ-ዐለመ ያስፈልገናል፡፡ ይህ ግንዛቤም ከቅማችን በላይ ያለውን ጋርዶ ያሳያል፡፡ (ለምሳሌ፣ የህይወትን ትርጉም እንፈልግ ብንል፣ ህይወት ጥቅም አልባነች ብንል)፡፡ ከግርዶሹ በላይ መመልከት አንችልም፡፡ ላካን መሰል ልምዶችን trauma of the real ይለዋል፡፡ ይህ ማህበራዊ ትርጉሞች ትክ ትርጓሜ ስለሌላቸው ህመም ፈጣሪ ናቸው[8]፡፡

እንደ ታይሰን (2006፡33) በላካንያን መነፅር የሚደረግ የሥነ-ጽሁፍ ትንተና ሶስቱ መሪ እስቦች ከድርሰቱ በማፈላለግ መሆን እንዳለበት ትመክራለች፡፡ እንዚህም እንደሚከተለው ትዘረዝራለች፣

7

8 የላካን የፍካሬልቦና ግንዛቤና እስብ ጥልቅ፣ ሰፊ፣ ተቀያያሪና አወዛጋቢ ነው፡፡ አይደለም እኔ በላካን ላይ የጻፉትም ይህን ከመጠቆም አልቦዘኑም፡፡ ስለሆነም፣ እስቡ በገባኝ አቅም በእስቦቹ ተጠቅሜ ትንታኔ ለመጠቀም ያላሰለስ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ሆኖም፣ የደረስኩበት ድምደሜ የመጨረሻ ሳይሆን የመጀመሪያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው መሆን ያለበት፡፡ አሁን በዚህ ፅሁፍ ከቀረበው በተጨማሪም ሰፊ ግዜ በመውሰድና ጥልቅ ተመስጦ በማድረግ ሃሰቤን በተሻለ መረዳትና ትርጓሜ ለመቅረብ እሞክራለሁ፡፡

*I. Do any character, event, episodes in the narrative seem to embody the Imagery Ordere, in which case they would involve some kind of private and either fantasy or delusioned world?*
*II. What parts of the text seem formed by the Symbolic Order? That is where do we see ideology and social norms in control of characters beha and narrative events?*
*III. Does any parts of the text seem to operate as a representative of the Real, of that dimension of existence that remains so terrifying beyond our ability to comprehend it that our emplse is to flee it, to repress and deny it?*

በመቀጠል የታይሰንን ምክር በተከተለ መንገድ በ‹‹መረቅ›› ከመጡት ገፀ-ባህሪያት የህይወት ልምድ ሃቲት መመርምር ይቻላል፡፡ ትንተናችን ከክሰተቱ የሚቀጥልና የጥናቱን ግብ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ልብ ይሉዋል[9]፡፡

### 4.1. ክስተተአንድ፡አላዛርሥነ-ልቦናዊሁኔታትንታኔ

> *የሚያነጋግረኝ ሰው እፈልግና ስወጣ ባገኝም ዝም እላለሁ፡፡ ...ከክፍሌ ልጆች ጋር በአፍ መላፋት የምወደው ልጅ ተዘግቼ ወጥቼ ተዘግቼ የምገባ ሆንኩ፡፡ የማየው ነገር ሁሉ ምንም አልጥምህ አለኝ፡፡ ከአንዳንድ የትምህርት ቤት ጓደኞቼ ጋር የለመድናቸው የድሮ መዝናኛ ቤቶች የተሸሹ ይመስላሉ፡፡ ‹የት ጠፋ› እላለሁ እኛ እዛ ወንበር ጋር ቀልድ ስንተረትር ጮክ ብሎ ‹እሱን ጆክ ሰምቼው ነበር› የሚለው ያልተጠየቀ ተሳታፊ፡፡ ማን መከረው እንዲሰወር እኔ ከተባራኪ ሌላ ባዶ ነኝ፡፡ ያለደኞቼ--ያለ እሱ ያለ እሱዋ ያለ ሌላውም ባዶ ነበርኩ፡፡ ሳፊ ወተት ተደግፈን የዊኒስተንና የኬንት ቁሩ እየተቀባበልን የጤስነው ጉዋደኞቼ ሁሉ ሕይወቴ ናቸው፡፡ ...በዛን ሰሞን ከምሽቱ አራትና አምሰት ሰዓት በእግሬ ከአራት ኪሎ ቤቴ እሄድ ነበር ፡፡ አንድ ሁለት ቀን አብዮት ጠባቂዎች አቁመውኛል፡፡ ተበርብሬአለሁ፡፡ አቆሙኝ ቦታ ቢረሸኑኝ ግድ አልነበረኝም፡፡* ***<u>...የተዘረፍኩትን መረቅ .... እረፍትንና መዘንጋትን ፍለጋ...</u>****አራት ኪሎ ከጭቁን ህዝቦች ጋር ወይ ከብኩናን ነገር ጠጅ በብርሌ ነፋሁ...በሲኒማ ቤቶች የሸራ ወጋገን የቀያይ ልጃገረዶችን ምላሰ.....በቀይ መብራት ፍም የቀዘቀዘች ሴት ግንባር ጠባሁ.....ገበረ ተንሳይ ኬክ ቤት በረንዳ ላይ በወንበር ስር ጭን ያዝኩ፡፡ ... ባለጌ ሌላ ቡታ ሂድ ተባልኩ፡፡ ... ርካሽ አልጋ ላይ ከምንመሳሰል እህቴ ጋር ወደቅሁ....ምንም ከማይገባት ከተደበረች ለግላጋ ጋር ወይም በደረቅ ሌሊት ከሆነች አይኖቹዋ በስካር ካፈጠጡ ሸሌ ጋር ተጋድሜ አልፎ አልፎ የምሰማው የጠመንጃና የሽጉጥ ተኩስ እንዳነሳው የሚገፋፋኝ ጥያቄ፡ለመሆኑ ማነው የተኮሰው ? ለምን ተኮሰው ? ተኩሱ ማን አለ?እነዲተኩሱ የነገራቸው ማነው ?እኔ ከተኳሹና ከተተኮሰበት የተለየሁ ኖሬለሁ ?እስከዛሬ ጠላቴ ማን ነበር ?እሰከ ዛሬ ጠላቴ ሳይሆን እንዴት በአንድ አመት ወይም በሁለት አመትውስጥ ጠላቴ መሆኑን አወቅሁ?እንዴት ሊሆን ቻለ...?* (ገጽ 138-140፣ ሰረዝና አጽኖት ከእኔ ነው)

*መነጋገር*፣ *መጫወትና ማውራት ሲፈልግ* የተመልከትነው አላዛር ከአብዮቱ መምጣት በፊት በከፍተኛ ሁኔታ ከጓደኞቹ ጋር የነበረው በእብደት የታቃኘ የልጅነት ደስታ ውስጥ አልፎ መምጣቱን ተመልከተናል፡፡ አሁን በአብዮቱ ወቅት ግን ይህን ፍላጎቱ እውን ማድገረግ አልቻለም፡፡ አንድ አላዛር ብቻውን አጠገቡ የሌሉ ጓደኞቹን በለሌሉበት እንዳሉ አድርጎ ሲቃዥ እናገኘዋለን፡፡ ይህም በላካን እሳቤ መሰረት ሥዕላዊ ስርዐት በሆነው የአዕምሮ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኝ ይነግረናል፡፡ ይህ የስነ-አዕምሮ ይዞታ የሚወክለው በጨቅላነት ዘመናችን እኛነታችን ከእናታችን ጋር የተቃለጠበትን/ የተዋሃደበትን የሙሉ ሃሴት ወቅት የሚወከልበት ሲሆን ወቅቱ ለቋንቋ ባዕድ የነበርንበትም ነው፤ ለጨቅላው እናት ፍፅምናው (አዳኝ፣ ጠባቂ፣ ተፈጥሮና ፈጣሪ) የሆነችበት ነው፡፡ ወቅቱ እጅጉን ቅዠታዊ ቢሆንም እጅጉን ሃይለኛና በገነነ እርካታ የተሞላ ነው፡፡ (ታይሰን) በዚህ ግንዛቤ ወደ ድርሰቱ ብንመለስ፤ አንድም አላዛር ቋንቋን በስራ ላይ አለማዋሉን እናገኛለን፡፡ ሁለትም አላዛር ካለጓደኛቹ ባዶ መሆኑን በተደጋጋሚ ማሰቡን እንመለከታለን፡፡ ሶስትም አላዛር ባሌለ ነገር ሲቃዥ እናገኘዋለን፡፡

---

[9]ትንተናዬ በአላዛር የተወሰነ ይሁን እንጂ፣ የሰነድ ፍተሻዬ ተመሳሳይና እጅግ የበረታ ትንተና ማድረግ ይቻላል፡፡ ሆኖም የቦታና እጥረት በዚያ ረግድ ከመግፋት ቆጥቦኛል፡፡ ምልከታዬን በክስተቱ የሥነ-ትርጓሜ ሃተታ በመጠኑ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡ በመጨረሻ የገፀ-ባህሪያቱን ሥነ-ልቦናዊ ሁኔታ አስመልክቼ የማቀርበውን ድምዳሜ በአሉታ ሊጎዳ ይችላል፡፡ ነገር ግን በውይይት ሊዳብር የሚችል እንደሆነ ከወዲሁ መግለጽ ሊኖርብኝ ይችላል፡፡

ይህ ህመም ሲሆንበትና ከዚህ ህመሙ እራሱን ለማከም ሲዳክር ነው የምንመለከተው፡፡[10] «***...የተዘረፍኩትን መረቅ .... እረፍትንና መዘንጋትን ፍለጋ...»*** የሚለን ይህን ለፈውስ የሚደረገውን መዳከር ነው፡፡ በመቀጠል በሚመጣው የተረኩ ክፍል የምናገኘው አላዛር እራሱን ለማከም ያደርገው መዳከር ወደ ስርዐተ ማህበር ወደ ቆመበት የህግ ቦታ ማለት አባታዊነት ወደ ወደ ነገሰበት ስፍራ ሲገባ ነው፡፡ ይህም በቋንቋ መቻል የሚዳኝ ነው፡፡ ጨቅላው የራሱ ማንነት እንደለው የሚረዳበትና ይህን መረዳቱን በትርጉም ከእናቱ ለይቶ በአባቱ ስርዐት ተረጉሞ በመበየን የሚፀናበት ነው፡፡ ከዚህ ቅዠታዊ አለም ሲወጣ ወደ ስዕላዊው አለም ይሸጋገራል፡፡ ይህ አለም ክልከላ ያለበት ነው፡፡ አላዛር እራሱን ላዳን የረገጠባቸው ቦታዎችና የወሰዳቸው ፈውስ የማሻት እርምጃዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

1. *አራት ኪሎ ከጭቁን ህዝቦች ጋር ወይ ከብኩናን ነገር ጠጅ በብርሌ ነፋሁ... 2.*
2. *በሲኒማ ቤቶች የሸራ ወጋገን የቀያይ ልጃገረዶችን ምላሰ.....*
3. *በቀይ መብራት ፍም የቀዘቀዘች ሴት ግንባር ጠባሁ.....*
4. *ገበረ ተንሳይ ኬክ ቤት በረንዳ ላይ በወንበር ስር ጭን ያዝኩ፡፡ ...*
5. *ባለጌ ሌላ ቡታ ሂድ ተባልኩ፡፡ ...*
6. *ርካሽ አልጋ ላይ ከምንመሳሰል እህቴ ጋር ወደቅሁ....*
7. *ምንም ከማይገባት ከተደበረች ለግላጋ ጋር ወይም በደረቅ ሌሊት ከሆነች አይኖቹዋ በስካር ካፈጠጡ ሸሌ ጋር ተጋድሜ አልፎ አልፎ የምሰማው የጠመንጃና የሽጉጥ ተኩስ እንዳነሳው የሚገፋፋኝ ጥያቄ፡*

ከላይ የተመለከቱት 7 ቦታዎች የላዘር ፈውስ ለማግኘት የዳከረባቸው ናቸው፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ አላዛር የሚፈልገው ያጣቸውን ጓደኞቹን በተለይም የቅርቡ ፍቅረኛው የሆነችውን ተባራኪን ነው፡፡ ተባራኪ ደግሞ ሙሉ በሙሉ በስዕላዊው አለም ቁጥርጥር ስር ወዳቃለች፡፡ የዘመኑ አይዲዎሎጂ የሆነው የማርክስ ረዕዮተ አለም ጠልፎ ወስዷታል፡፡ ይህን የተባራኪን ሁኔታ ከማርከስ እምነት መከተል ጋር አያይዘን ከስተን ተመልክተናል፡፡ ይህም ዕምነት ሆኖባት ተገዳ ከአላዛር ጋር ማውራት መነጋገር እዳትችል አደረጋት፡፡ በዚህ የተነሳ አላዛር ይዳክራል፡፡ ይዛክራል፡፡ በመጨሻም ሁሉም አልሆን ሲለው መኖር ትረጉም ያጣበታል፡፡ ለህይወት መሳሳት ይሰወርበታል፡፡ የማይችላቸውን እና ከእይታው ውጪ ስለሆኑ ነገሮች ይጨነቃል፡፡ ይህ በላካኒያኑ እሳቤ አላዛር በስነ-አዕምሮ ደረጃ እውነታው አለም ውስጥ መገኘቱን ያስረዳል፡፡ ምክንያቱም በዛ አብዬት የሰው ልጅ እንደ ሾላ በሚረግፍበት ወቅት ከአራት ኪሎ ወደ ተባረኪ ወደ ሰፈሩ ሲመጣ «ቢረሽኑኝ ግድ አልነበረኝም» የሚለውን ይዘን በመጠይቅ የመጡት መልስ ሊያበጅላቸው የመይችላቸው ጥያቄዎች የሚያስረዳን የእውነታ አለምን ይሆናል፡፡ [11]

ስለ አላዛር ስነልቦናዊ ሁኔታ መጠነኛ ግንዛቤ ከያዝን ወደ የልጅነት አብሮ አደጉና ፍቅረኛው ተባራኪ ሥነ-ልቦናዊ ሁኔታ ቀጥለን እንከስት፡፡ ይህ ክስተት በመጋቢት 1969 የተባራኪ የወጣቶች ሊግ ሰላማዊ ሰልፍ ባደረገበት ሌሊት የተፈጠረ ነው፡፡ ተባራኪ ሰላማዊ ሰልፉን ለመሳተፍ ፈረታ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህን ፍራቻዋን ለትግል አጋሯ አማን (የእሷም፣ የአላዛርም አብሮ አደግ) አትነግረውም፡፡ ይህን ፍራቻ «(ፈሪው ወዳጄ አላዛር በልቤ ጥርጣሬ አስገብቶ

---

[10]በላካን እስብ ውስጥ ፅነሰ-ሃሳብ አዘል ቃላት ላይ ሰፊ ትንተና ያቀረበው ኢቫንስ In Lacanian terms, the paranoiac lacks the NAME-OF-THE-FATHER, and the delusion is the paranoiac's attempt to fill the hole left in his symbolic universe by the absence of this primordial signifier. (Evans, Dylan, 1996:36)፡፡ ይህ አባታዊነት ዋና መገላጫ በመሆን ሌሎች መገለጫዎችን እንድናፈልቅ ይሆናል፡፡ ይህን አባታዊነት ማጣት ማለት ስርዐተ ማህበሩ ማጣት፣ ማንነትን ማጣት ሲሆን ይህም የተቃወሰ ስነልቦናን ያመጣብናል፡፡ የበለጠ ግልፅ ሳደርገው፣ በአባታዊነት ከተቀመረው ስርዐት(ሲምቦሊክ) በእናታዊነት ወደ ተቀመረው ስርዐት (ኢሜጅሪ) እንመለሳለን ማለት ነው (Evans, 121) ። እንዳየነው ጨቅላው ከእናቱ በተዋሃደበት የፍጹም ሃሴት ግን የቅዠት አለም ውስጥ ማንነት እራሱን ችሎ አይመጣም፡፡

[11]*ክስተተ ሁለት፡ ተባራኪ ሥነ-ልቦናዊ ሁኔታ፣* ክስተተ ሶስት፡ ማከዳ ሥነ-ልቦናዊ ሁኔታ፣ ክስተተ አራት፡ እዝራ ሥነ-ልቦናዊ ሁኔታእያልኩ በዝርዝር ለመቅረብ ይቻል ነበር፡፡ ነግር ግን ቦታ ገደብ ሆኖኛል፡፡ ይህ የፅሁፌ ክፍተተ ነው፡፡ ይህን ክፍተተ ወረቀቱን በማቀርበበት ወቅት ለመሸፈን ይሞከራል፡፡ በውይይት የሚዳብሩ ስነትርጉማዊ ጉዳዮችም አይጠፉም፡፡ በተጨማሪም በአዳም ረታ መረቅ ላይ ጥልቅ ያልኩትን ጥናት እያደረግኩ ነው፡፡ ይህን ፅሁፍ የዛ ጥናት አካል ተደርጎ ይገምገምልኝ፡፡

ሳይሆን ይቀራል) ለአማን ልነግረው አልደፈርኩም፡፡ ግን ደግሞ የጠላቴን አይን ዕያየሁ ግንባሩ ላይ መጮህ እፈልጋለሁ..... አዳም፣ 2007፤ 242፡፡» ከዚህ ፍላጎት ተነስታ ወደ ሰልፉ፣ ሰልፉን ተከትሎም ሽሽት ይመጣል፡፡

*ከሁሉ ለመሸሸ የምችል አይነት ወደ አማን ደረት ተጣበቅሁ፡፡ አማን ጓደኛዬ ነው፣ ጓደኛዬ ነበር፣ እና ምን አለበት? አይኖቼን ገርበብ አድርጌ አላዛርን አሳባለሁ፡፡ አላዛር አይኖቹን ጨፍኖ እየተልቆሰቆሰ ሲያቅፈኝ፡፡ በፀሃያማ ቀን በቀስታ ታኮኝ ሲቆም፡፡ በሃሳቤ እዛና እዛ ስቀባዠር አማን አናቴን ሲስመኝ ሰማሁት፡፡ አላዛርን ማለም አቆምኩ፡፡ ግራ በመጋባት ምልክ ቀና ብዬ አየሁት፡፡ ቀና ብዬ እያየሁት ሳለሁ ሳልጠብቀው አፌ ላይ ሙሉ በሙሉ ሳመኝ፡፡*
*በፍጥነት ከእቅፉ ተላቀቅሁና ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ቆም ብዬ ጃኬቴንና ሱሪዬን አስተካከልኩ፡፡*
*«የተ ነው?» አለኝ*
*«ቤት ለመሄድ ነበር» ተራዬ እንዳልሆነ አውቃለሁ*
*«መኪና የለም፡፡ ትንሽ ረጋ በይ፡፡ ተራሽ ገና ነው»*
*የምመልሰው አልነበረኝም፡፡...*

ልብ እንድንለው የሚገባን ነገር ይኖራል፡፡ ይህም የክስተቱ ባለቤት ተባራኪ **ሽሽት** ወስጥ መሆኗ ነው፡፡ የምትሸሸው ወደ አማን ደረት ነው፡፡ ከአማን ደረት ሳታውቀው በልቦናዋ ወደ አላዛር ትመነጠቃለች፡፡ ይህ ተባራኪን በቋንቋ ከተበየነውበአባታዊነት ከጸናው ከትዕምርታዊ አለም ነቀሎ በቅዠት ወደ ተበየነው ሥዕላዊ አለም ይተክላታል፡፡ በዚህ ግዜ የሌለውን አላዛርን ፍለጋ ስትዳክር ተመልክተናል፡፡ በመጨረሻም፣ መልስ እንዳጠች አይተናል፡፡ ተባራኪአማን ጃኬት እና ሱሪ ሲነካካ አይታወቃትም፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ በስዕላዊ አለም ውስጥ መዋጧን የሚስረዳን ነው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ መታየት ያለበት የአማን ሁኔታ ነው፡፡ አማንንከንፈር እስከመሳም ያደረሰው ሁኔታ ሁለቱም በተመሳሳይ ስሜት ውስጥ መውደቃቸውን የሚያስረዳ ነው፡፡ ምክንያቱም፣የጓደኛን ፍቅረኛ የሚፈቅድ ትዕምርታዊ ስርዐት/ህግ የለምና፡፡ ነገር ግን እያወቀ ይህን ፍትወት መር ድርጊት ማድረጉ እሱም በቅዠቱ መዋጡን ያሳያል ማለት እንችላለን፡፡

የሰላማዊ ሰልፍ ማግስት ትውስታዋ የሚነግረን ተባራኪ ከአላዛርና ከእናቷ ጋር መሆኗን እንረዳለን፡፡ «የሰላማዊ ሰልፉ ማግስት በመሸሸ ላይ እያለሁ፣ ትዝ ያሉኝ ብቸኛ እናቴና አላዛር ነበሩ፡፡ ለብቻዬ በኮሮኮንች ላይ እየተወለካከፍኩ ስሮጥ የከበበኝ ጨለማ ማሃል ያታወሱኝ እማማና አላዛር ነበሩ፡፡ <u>ፍቅር ከዋናው አላማዬ በላይ የሚናሳፈፍ ጉድ የለውም</u>፤ (ሰረዝ የኔ ፤አዳም፣ 246)፡፡ ይህ ክስተተ በራሱ ተባራኪ በቀውጢ ሰዓት ችንቀት ውስጥ በመደቀችበት የአብዮት ወቅት በስዕላዊ ደረጃ መውደቋንና ይህም ለአላዛር እና ለእናቷ ያላትን እሷ በጥዕምራተዊው አለም ስነ-ልቦናዋ ልትፈቅደው እንደማትፈል ያሳያል፡፡ ለዚህም ለፍቅር ቦታ ነስታዋለች፡፡

ይህ የሚሆንበት ምክንያት ተባራኪ ሙሉ በሙሉ በማርክስ አይዲኦሎጂ ቁጥርጥር ስር በመውደቋነው፡፡ ይህም ተባራኪ ስለማርክስ ኣዳኝነት እና ፈዋሽነት በመሰበኳና በማመኗ የራሷን ተራክ ለመስራት በመነሳቷነው፡፡ ተባራኪ «ችግሩ አላዛር ከታሪክ ውጭ ሆኖ ነው የሚያየኝ፡፡ እኔ ደግሞ ታሪክ ልሰራ እየለፋሁ ነው፡፡ ግዜዬን ለጭቁን ህዝቦች ነጻ መውጣት መስጠት ነበረብኝ፡፡ ለምወደው ድርጅቴ መስጠት ነበረብኝ፡፡»(አዳም፣ 242)፡፡ በመሆኑም አላዛር ለተባራኪ የመያደፍር ‹ፈሪ› ወይም የማይገባው ‹ደደብ› ወይም «ከግል ስሜቱ መውጣት የከበደው ራስ ወዳድ ነው፡፡» (አዳም፣ 240) ፡፡ በዛው ሰሞን ውስጥ ተባራኪ ስለአማን በምታስብብት አላዛርን እንደ ሴት አድርጋው ስትተረከው እናገኛታለን፡፡ «አማን በአእምሮዬ መጣ፡፡ አላዛር የሆነ ሴታ ሴት መሰለኝ፡፡ የሆነ ያልወለደኝ እማማ፡፡ ጡት ባያጠባኝም የሆነ የወለደኝ ምንትስ፡፡ የምወደውን ልጅ ስሮጥና ስሸሽ አስታውሼው፣ ስረጋጋ፣ በዝምታ በልቤ እንዲ አላኩት፣ ማዘሬ ነህ ምንድነህ?» (አዳም፣ 248)፡፡ የምታቀርበው ጥያቄ ተባራኪ ግራ መጋባቷን ያሳየናል፡፡ ይህም በላካንያን እሳቤ በእውነታ የስነ-አዕመሮ እርከን ውስጥ መገኘቷን ጠቋሚ ነው፡፡

ተበራኪ እና አላዛር በሃላቸው በሚተኛው መለያያት ሳይነጋገሩ ቢለያዩም የጋራ ፍሬ ግን አፍረተዋል(ልጅ ወልደዋል)፡፡ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ተባራኪ ሌላ ባል (ፋሲልን) አግብታ ከልጇና ከባሏ ጋር ነች፡፡ ሆኖም አላዛርን ከመሻት፣ አላዛርን በአእምሮዋ ከመዝራት፣ አላዛርን በህሊናዋ ከመቆፈር አታመልጥም፡፡ ለምሳሌ፣ ሁለተኛ ልጇን በምትገላገልበት የምጥ ሰዓት «ጩኸቴ አፌን ለቆ ሲወጣ ‘ናልኝ’ ያልኩት ‘አላዛርን!’ ነበር፡፡» (አዳም፣ 307)፡፡ ትለናለች፡፡ ተባራኪ ህመምተና ነች፡፡ የቆመችበት የለችም፡፡

ይህ ሁኔታ በመረቅ በተደጋጋሚ የሚከሰት ነው፡፡ መሰል የስነ-ልቦና ወቀስ እጅጉን የገነነበት ብሎለድ ነው ማለት ድፍረት አይሆንም፡፡ መረቅ በእብዶችና በእብደቶች የተገነባ ነው፡፡ ስለዚህም ይህ ክፍል በእንጥልጥል የቀረ የሚቀጥል ነው፡፡

## 5. ክፍልአምስት፡መደምደምያ

ቋንቋን ከቃላዊነቱ አላቆ ወደ ጽሁፋዊነትና *ሥነ-ጽሁፋዊነት* ማሻገር መቻል በሰው ልጅ የስልጣኔ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራን ይዟል፡፡ *ሥነ-ፅሁፍ* በመግባቢያነቱ የምንፈርጀውን **ቋንቋ** በተለያዩ ቅርጾች፣ ስልቶች፣ እና *ሥነ-ዘዴዎች* እያረቀቀ እያበለጸገ የግለሰበን፣ የማህበረሰብን፣ እና የግለ-ማህበሩን ምንነትና ማንነት እንዲሁም የወደፊት እጣፈንታ ያቀርባል፡፡ *ሥነ-ጽሁፍ* ማንነት ይገነባበታል፣ ዘመን ከስፍራ ይታሰርበታል፣ ገለ-ማህበራዊ ስልጣኔ ይከሰትባታል[12]፡፡

በዚህ ግንዛቤ መሰረት ከተራመድን **ማንነት** በሁለት የተቆራኙና የማይነጣጠሉ የሆኑት ግለሰብና ማህበረሰብ ጥምር ጉዞ ውጤት ሲሆን *ሥነ-ጽሁፍ* በዚህ ቁርኝት ውስጥ ግለሰቡና ማህበረሰቡ በጋራ ለመራመድ የሚያደርጉትን **ሙግት** እናስተውልበታለን፡፡ በዚህ ማስተዋላችን ውስጥ በአንክሮ መመልከት ያለብን ጉዳይ የጥበቡ ከያኒ (ባለቅኔው፣ ገጣሚው፣ ወይም ደራሲው) አላማ ማህበሩን ወደ ተሸለ ግንዛቤና የኑሮ ዘይቤ ማምጣት መሆኑን ነው፡፡ በአጭሩ ከያኒው ገልባጭ ሳይሆን ፈጣሪና ለዋጭ ነው፤ (ቴዎድሮስ፣ 2001፤ 141)፡፡ ይህ ካስማማን፣ ከያኒው ከፍካሬልቦና እና ከ*ሥነ-ማህበር* ባለሙያው ጋር በአላማና ግብ ሰመረ፣ ተመሳሰል ማለት ነው[13]፡፡

ይህ ጥናት ክስተተአካልን ከፍካሬልቦና፣ ከሃዲስ ታሪካዊነት፣ እንዲሁም ከ*ሥነ-ሰብ* ሣይንስ ጥናት ጋር በማቀናጀት አዳም ረታ (2007 ዓ.ም.)**«*መረቅ*[14]»** ረጅም ልቦለድ ውስጥ በመጡ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ «ማህበረግለሰባዊ ማንነት

---

[12] *ሙከራዬ ወደ-መድረሻዬ መንደርደር እንጂ ሥነ-ጽሁፍን መበየነ አይደለም፡፡ ሥነ-ፅሁፉ የገለ-ሰቡን ተሞክሮ ከማህበረሰቡ ኑሮ እያከራከረ ያቀርባል፡፡ ግለሰቡ ለማህበረሰቡ የለውጥ ሃዋሪያ ነው ለማለት ያቻላል፡፡ ሕይወት ተፈራ (2012:423)ለውጥ የማህበር/ የመንጋ ሳይሆን የግለሰብ ጥርት ውጤት እንደሆነ ከህይወት ልምድ ተነስታ ጽፋለች፡፡(" … I concluded that it was individuals who changed the world for the better through their genius and inspiration…. I come to realize it was individuals who changed the society.") ነገር ግን፣ ማህበረሰቡ በግለሰቡ የሚኖረው ሃይል እጅግ የጠነከረ ነው፤ ግለሰቡን እስከ ማግለል፣ የግለ-ሰቡን ሰው መሆን እስከ መካድ፡፡ ይህም ያቃውሰዋል- ግለ-ሰቡ ይቀውሳል፣ ያብዳል፡፡ የግለ-ሰቡ መቀወስ የማህበረሰቡም መቀወስ ነው፡፡ እብደት የአማርኛ ሥነ-ፅሁፍ አንዱ መገለጫው መሆኑን ልብ ይሉዋል፡፡*

[13]*የፍካሬባለሙያና የሶሲዎሎጂስቱ አላማም በሁለቱ የማይነጣጠሉ ሃይላት መሃከል የሚኖረውን ግጭት በንግግር አለሳልሶግለሰቡን ጤነኛ ማህበረሰቡን ጤናማ ማደረግ ነው፡፡ እንደ ሆሴን* (Hosain) *እና አሊ* (Ali)*የሚያስማማው ህግ ልሂቃኑ ማህበራዊ ግዴታቸው የበዛ ሲሆን መብታቸው ግን እጅጉን ያነሰ መሆኑ ነው፡፡* (*"The* general rule is: the higher the status and culture of the individual are, the lesser his rights are and the greater his duties are." Hosain and Ali, 2014: 136) *ለዚህ ደግሞ የሃዲስ አለማየውን «ፍቅር እስከ መቃብርን»፣ የበዓሉ ግርማ «ካድማስ ባሻገር»፣ የዳኛቸው ወርቁ «አደፍርስ» እና የሥብሃትለአብ ገ/እግዚሐብሄር «ሌቱም አይነጋልኝ» ጥሩ ማሳያዎች ይሆኑኛል፡፡ ደራሲያኑ በትምህርት እውቀት እናበማህበራዊ ልምድ ከማህበረሰባቸውይልቃሉ ወይም ይለያሉ፡፡ የደራሲያኑ ልቀትና ልዩነት  የማህበራቸውን መፃኢ እድል ለማሻሻል፣ለመለውጥ አጥብቀው ሞግተዋልና፡፡ ማህበራቸውም ቁፎውን ስለነኩበት አመድ አፋሽ ያደርጋቸዋል፤ ይገፉቸዋል፣ ያጠፉቸዋል፡፡ እንደግለ-ሰብ ደራሲያኑ በነብስያ የሉም፣ ማህበራቸው ግን ከሃሳባቸው ጋር ዛሬም ትግል ላይ ነው፡፡*

[14]*መረቅ፣ ሃገራችን የኃይለ ሥላሴ ዘውዳዊ ስርአት ማክተም ተከትሎ የመጣውን በተለምዶ በደርግ በሚታወቀው ወታደራዊ ስርአት ማግስት የነበርንበትን የማህበረሰባዊ ለውጥ ሁኔታ አብይ ጉዳዩ ያደረገ ልቦለድ ነው፡፡ ይህ ዘመን ሃገሪቱ ማህበረሰባዊ አብዮትን ያስተናገደችበት ታሪክ አካል ነው፡፡ ዘመኑ ወዲህ በ«ማይታረሰው ሰማይ» የተመሰለው የንጉሱ ስልጣን በገበሬዎች አመፅ፣ በታክሲሹፌሮች እንቢታ፣ በጦር ሰራዊት የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ፣ በተማረው የህብረተሰብ ክፍል ስራአጥነት ምሬት ወዘተ. ተሸርሽሮ በመጨረሻም የስራዓቱ ጠባቂ በነበረው የወታደሩ ነፍጥ ስርአቱ  ያከተመበት ነው፡፡ ወዲህ  በንጉሱ ግዜ የ«መሬትላራሹ›› ጥያቄዎችን እንደ «ኢጋሊቴ-ፍራተርኒቴ-ሊበሬቴ» ማህበረዊ እና ግለሰባዊ ምናቦችን ለመቀዳጀትየወጠኑ የዘመኑ ምሁራን «ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም» በማለት በተደራጀ መልኩ የስልጣን ባለቤት ሆኖ*

አመሳሰልን» ለማሳየት ያለመ ነው፡፡ ጥናቱ የአዳም ረታን የአብዮቱ ዘመንኛ ማህበራዊ ወጣቶችን የማንነት ብያኔን በተንታኝ ሥነ-ትርጉማዊ ክስተተአካል የጥናት ሥነ-ዘዴ ለማሳየት ያለመ በመሆኑ ከነባር ግንዛቤዎች ጥልቅ አረዳድ ይዞ እንደሚመጣ ታምኖበታል[15]፡፡ ሃርማንን አጣቅሶ ካፍሌይ (2001፡ 189) እንደሚያስረዳው ሥነ-ዘዴው ጥልቅ ትርጉም በመስጠት ሂደት ውስጥ ትርጓሜው የሚፈልቅበትን ሕይወት መር ተሞክሮዎች በማመላከት አካሉን በምንነቱ በመበየን በዋና/መሰረታዊ ባህሪው ያሳያል፡፡ ይህም የተዘነጋውን ወደ እይታችን በመመለስ አዲስ/የተሻለ ብያኔ ይዞ ብቅ ለማለት ያስችላል፡፡

በሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ የሥነ-ጽሁፍ ትምህርትና ጥናት መስክ ቀደምት እንደመሆኑ ወዲህ ያበረከተው ሃገራዊ ፋይዳና ወዲህም ያደረገው እድገት ያልተነካ ጥሬ የጥናት መስክ ነው[16]፡፡ የሆነው ሆኖ የአሁኑ ጥናትየሥነ-ጽሁፍእናየቋንቋጥናትበአገራችንሁለንተናዊእድገትሊወጣየሚችለውንሚናእናተግባርያመላክታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በዚህ ጥናት እምነትን እንደ ማህበረሰብ ስነ-ምግባር ግንባት ምንጭ አድርገን በመውሰድ አይተናል፡፡ የክርስትና እና የማርክስ እምነት ተከታይ የሆነው ማህበረሰብ እምነት ቅዱስ እና እርኩስ በሚሊ አይነኬ ድንጋጌዎች በመዋቀሩ በድብቅ ሲጥሱት ተመለክተናል፡፡ ይህ ለእለምነት ስነምግባር ያለመገዛቱ ማህበረሰቡ ጤናማ እንዳልሆነ ተደርጎ ተተርጉሟል፡፡ ምክንያቱም፣ የማህበረሰብ ሳይነስ ባለሙያዎችን ግንዛቤ ከግምት በመውስድ እምነት ማህበራዊ ቦታውን ለሌሎች ማህበራዊ መዋቅራት እያሸጋገረ ምክንያታዊ የሆነ ማህበረሰብን እንደሚገነባ ሃተተ ያቀርባሉ፡፡ የምክንያተዊነት መገለጫ ደግሞ በውይይት ላይ የተመሰረተ የተሸላ ምቾት ና ስምምነት የሚሰጠውን የመውሰድ ሂደት ነው፡፡ ይህ ለምዕራባውያኑ የሚሄድ ሲሆን በምስራቃውያኑ ዘንድ (የአረብ አጋረት፣ ቻይና፣ ታይላንድና ህንድ ወዘተ) እምነት ማህበራዊው ፋይዳ ይበለጥ እየተጣነከረ የማህበረሰብ ግንባታውም በዕምነቱ የባላይ ተቆጣጣሪነት የሚሄድ ነው፡፡ ወደ ድርሰቱ ስንመለስ ግን ሁለቱንም ሂደቶች ባማጣት ከእምነትም ከምክንያትም የወጣ ማህበረሰብ እንመለከታለን፡፡ ይህም በምቾት በማጣት የተቃወሰ ማህበረሰብ ያደርገዋል፡፡

የግለሰብን ስነልቦና ሁኔታም ለማሳይት በተደረገው ሙከራ ሁለት ገፀ-ባህሪያትን በመውስድ የተደረገው ጥናት እንደሚጠቁምን ግለሰቦቹ በስነ-አዕምሮአዊው ደረጃቸው ጤናማ እንደልሆኑ ነው፡፡ እዚህ ጋር ጤናማ የስነ-ልቦና ደረጃ የሚባለው ምን አይነት ነው ሊባል ይችላል፡፡ መልሱ ደረጃው ይለያያል፡፡ የላካን ና የፍሮይድ እሳቤ የሚመሳሰል ሲሆን በመሰረታዊነት የሰው ልጅ የሚመራው በኢ-ንቁ አዕምሮ ነው በሚለው ይፀናሉ፡፡ በመሆኑም ይህን የዐዕምሮ ክፍል ማጥናት ይገባል፡፡ እናም በእሳቤው መሰረት ከሄድን በዚህ የአዕሞሮ ክፍል እና በንቁ የአዕምሮ ክፍል በሚኖር ስምምነት ላይ የተመሰረተው ጤናማ ሲሆን በሁለቱ መሃከል ያለው ዝምድና የሚጠፋው ግለሰቡ እራሱን በሚትበት ወቀት ሙሉ በሙሉ ወይ በስዕላዊ አለም ይወድቃል፣ ወይ በትዕምርታዊው አላም ይወድቃል ወይ ደግሞ በእውነታው አለም ይወድቃል፡፡ ይህን የተበጠሰ ትስስር ለመፍጠር ቋንቋ ወሳኝ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰርት ተባራኪና አላዛር ጤናማ እንዳይደሉ፡፡ ሃሳባቸውን መግለፅ እንዳላቻሉ ተመልክተናል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ተባራኪ እራሷን

---

*የወጣው ወታደራዊው ደርግ ሥርዐት ከባድ ተቃውሞ አንስተው ከስርዓቱ ጋር (የሃይል ሥልጣን) ግብግብ የተካሄደበት ነው፡፡ ወዲህም፣ ወታደራዊ ስርዓቱ በሶሻሊዝም ንድፈ-ሃሳቦች እየተመራ በመላው ሃገሪቱ አብዮታዊ ለውጦችን ያደረገበት ነው፡፡ ወዲህም፣ ተቀናቃኝ የነበሩትን ምሁር መር ወጣቶች በፋሽስታዊ ጭካኔ መላ ሃገሪቱን በደም አበላ ያጥለቀለቀበት እና የንጉሱን ዘመን ባለስልጣናት እና የጦር መኮንኖች/ መሪዎች ያለፍርድ ሂድት በጅምላ የረሸነበት ዘመን ነው፡፡ ታዲያ* ጥናቱ «በረከተ-መርገም» በሆነው የዘመን ወቅት ውስጥ ያለፉት ወጣቶች ሥነ-ልቡናዊ እና ማህበራዊ እና ሥነ-ምግባራዊ ማንነት አመሳሰል ምን እነደሚመስል ያሳያል፡፡ መከሰትና ማሳየት ምን ለያቸው? እርግጥጥልቅ ጥናት ይፈልጋል፡፡ ብቻ የእኔ ጨዋታ ከመረቅ ጋር ነው፣ ይህ ማለት ግን ታሪክ ጋር ይሁነኝ አቆራኛለሁ፣ ከማህበረሰብ ጋር እገባለሁ፣ ግለሰብ እሆናለሁ (ሥነ-ምግባርም አዳብራለሁ) …፣፣፣…ዘመድ፣ ጎረቤት አፍርቼ ግለ-ማህበረሰብም ሆኛለሁ፣ ፡፡

[15] *የ1966ቱ ማህበራዊ ለውጥ የፖለቲካ፣ የታሪክ፣ የማሕበረሰብ ሳይንስ፣ የኢኮኖሚ? እና ሥነ-ፅሁፉ (ደራሲያንን እና ሃያሲያንን)፣ የፍልስፍና ምሁራንን አትኩሮት ያገኘ በመሆኑ ጉዳዩ አዲስ አይደለም፡፡ የሆነ ሆኖ ጥናቱ በቋንቋ አጠቃቀሙ ሆነ በሚያነሳቸው ዕርሰ ጉዳዮች እና በሚጠቀማቸው ድህረ-ሂሳዊነትን ልብሳቸው ባደረጉ የትረካ ቴክኒኮችን እየተገለገለ በአማርኛ ሥነ-ፅሁፍ እድገት ላይ ጉልህ አሻራዎችን እያተመ እንደሆነ የተመሰከረለትን ደራሲ ወጥ ሥራ መርምሮ አዲስ ግኝትን ያለመ ነው፡፡*

[16] ቋንቋና የቋንቋ ጥናት (ቋንቋ <u>የቃላዊነት ፅንሰ-ሃሳብን</u> ይሸከምልኝ) እንዲሁም ጽሁፍና የሥነ-ጽሁፍ ጥናት መቼውንም ቢሆን ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ቁምነገር ነው፡፡ ምክንያቱም ያለሃሳብ ወደ ቁስ ቴክኖሎጂ የምናደርገው ሽግግር የሰመረ ስለማይሆን ነው፡፡በዚህ ረገድ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ መበልጸጊያ ተቋም በኩል እየከወነ ያለውን «ጀብድ» የሚያስመሰግን ነው፡፡

በትዕምራታዊው አለም ስለምትዋጥ ነው፡፡ በመሆኑም የአላዛር ቋንቋና ፍላጎት ገሸሽ ታደርጋለች፡፡ አላዛርም በበኩሉ ሙሉ በሙሉ በሥዕላዊው የአእምሮ ደረጃ ስለወደቀ ያንን ፍላጉቱን ለማርካት ሲዳክር ተመልክተናወል፡፡ ይህም ነባራዊ የሆነውን የትዕምርታዊ አለም ስርዐት እየስረሳዋል፡፡ በላካን እሳቤ ስናስረው፣ የሰው አዕምሮ የሚሰራው በመገጫዎች ቅጥልጥል chain of signifiers ሲሆን የቅጥልጥሉ ፍሰት ጤናማ የሚሆነው በሶስቱ ደረጃዎች የሚኖረው መግባባት ላይ ያርፋል፡፡ ነግር ግን ከሁለቱ ገጸ-ባህሪያት ከዚህ ውጭ ናቸው፡፡

ማንነት በማህበረሰቡ፣ በግለሰቡ በተወሰነ ግዜና ቦታ የሚወሰን ነው፡፡ ይህን ከላይ ከደርስናባቸው ትንታኔዎች ጋር አይይዘን የምናገኘው የተቃወሰ ምህበረሰብ እና የአበደ ግለሰብ በእብየት ዘመን ይሆናል፡፡ ይህን ግንዛቤ ከታሪካ እውነታ ጋር ስናስተያየው ምልሳችን ውሃ የሚያነሳ ይሆናል፡፡ ይህም ሃገራችን ላለችበት ነባራዊ ገፅታ መፍትሄ ፍለጋ ሥነፅሁፍ ጥሪውን ለስነ-ሰብ፣ ለስነ-አዕምም፣ ለፈላስፋው፣ ለታሪክ በለሙያው ሲቅርብ እንደኖረና አሁንም በበለጠ ሁኔታ የድርሻውን እበረከተ እንደለ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ይህን ጥበብ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መተርጎመ ጥቅም ላይ ማዋል የሁሉም መሆን ይገባል፡፡ በዕርግጥ አንድ ነግር ልብ እንበል፤ ይህ ጥናት በራሱ በቂ አይደለም፡፡ ነግር ግን ጥሩ መንደርደሪያ ነው፡፡  ጥናቱ በይነ-ዲስፐሊናዊ የሥነ-ጽሁፍ ጥናት አገልግሎቱ ጥሪው ለራሱ ለሥነ-ጽሁፍ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ጥናት መስኮች ጭምር እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣  በጥናቱ የዘነጋነውን ወይንም ያለፍንበት የማይመስለንን እውነታ እንከልስበታለን፡፡ ይህ ከታሪክ ምልከታ ጎን ለጎን አሁን ላለንበት ሃገራዊ በሉት ገለ-ማህበረሰባዊ ማንነታችንን አመላካች ነው፡፡ ሌላው የጥናቱ ቁብ፣በደራሲው የምናብ ፍሬ እየታገዝን ጉዳዩን ባልታየበት መንገድ አመላክቶ የጎደለንን ለመሙላት መሞከሩ እና ስለድርሰቱ እና ዘመኑ ያለንን ግንዛቤ ለመፈተሽ እድል መፍጠሩ ነው፡፡ ጥናቱ ለሌሎች መሰል ጥናቶች በር ከፋች ከመሆኑም በተጨማሪ በጥሩ መንፈስ የታወደ የውይይት መድረክ እንደሚፈጥርም ይታመናል፡፡

## 6. ዋቢ መጽሀፍት


መረራ ጉዲና፡፡ 2005፡፡ *የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምሰቅልቅል ጉዞና የሕይወቴ ትዝታዎች፤  ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ እስከ ኢህአዴግ፡* አዲስ አበባ፣ ግራፊክ አታሚዎች

አዳም ረታ፡፡ 2007፡፡ *መረቅ፡፡* አዲስ አባባ፣ ሮኖቦት አታሚዎች፡፡

ቴዎድሮስ አለበል፡፡ 2006፡፡ *"ልጅነት" በማሕሌትና አለንጋና ምስር፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ (ያልታተመ የማስተርስ ጥናት)፡፡* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ 2001፡፡ *በይነ ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፡፡* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ 1948፡፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

ደበላ ዲንሳ፡፡ 2006፡፡ *ምቶ መኖር (ዱአኒ ጂራቹ)፣* ግለ ታሪክ፡፡አዲስ አበባ፣ ሮኖቦት አታሚዎች፡፡

Ema, T. 2007. Sociology, Religion, Development: Literature Review.Uiversity of Leeds, RaD: *Working Papers*. PP 4-27

Evans, D. 1996. *An introductory Dictionary of Lacanian Psychoanalysis*. London and New York: Routledge

Finlay, L. 2009. Debating Phenomenological Research Methods. *Journal of Phenomenology and Preactice*, Vol 3 No 1 pp 6-25

Habib, R. 2005. *A History of Literary Criticism: from Plato to the Present*. Oxford: Blackwell Publishing Ltd.

Hiwot, T. 2012. *Tower in the Sky*. Addis Abeba: Addis Abeba University Press

Itao, S. 2010. *Paul Recoer's Hermeneutics of Symbols: A Critical Dialectic of Suspicion and Faith. Kritike*, Vol 4 No 2. PP 1-17.

Kafle, P. 2011. Hermenutic Phenomenological Research Method Simplified. Bodhi: *An interdisciplinary Jornal*. Vol 5. Nepal, Kathmandu University

Mesay K. 2011. *Ideology and Elite Conflicts: Autopsy of the Ethiopian Revolution*. UK: Lexington Book

Moore, D. 2009. *Vision of Cultures: An Introduction to Antropological theories and Theoriesits*. 3rd Ed. USA: Althamrepress

Hosien Md.K, and Ali FMA. 2014. Relation between Individual and Society. *Open Journal of Social Sciences*. Vol 2, PP 130-147.

Qasi, A. 2011.Lacanian Concepts-Their Relevance to Literary Analysis and Interpretation: A Post structuralist Reading. The Criterion: *An International Journal in English*. Vol II, Issue. IV. PP1-12

Sumner, C. 1989. *The Philosophy of Man. Vol II: From Kant to the Situation in 1963*. India: Rekha Printers

Tyson, L. 2006. *Critical Theory Today: a User-Friendly Guide. 2nd ed*. NewYork & London: Routledge.

Harla Journal of Social and Behavioral Studies gives access to this work open access and licensed under a Creative Commons Attribution-NonCommercial 4.0 International License. (Creative Commons Attribution-NonCommercial 4.0 International License